ወርኃዊ ጥንቅር፣ ቅጽ 02 ቁ. 016
ግንቦት 2018 ዓ.ም እንደራሴ



# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ክራሞት

# እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

info@bridge-et.org

BRIDGE Research & Innovation - Parliaments. Peace. Policy

## መልክዓ - ብሪጅ

መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት አገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ የጥናትና ምርምር ተቋም ነው :: ብሪጅ፣ በዋናነት በኢትዮጵያ እና በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አባል አገራት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እንዲጎለብት እና ሰላም እንዲበለጽግ የሚሠራ ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ፖሊሲ ተኮር የጥናት እና ምርምር ተቋም ነው ።

## ተልዕኮ

ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ይጎለብት ዘንድ፣ ለፖሊሲ አወጣጥ ግብዓት የሚሆኑ፣ ተጨባጭነት ያላቸው ምርምሮችን ማድረግ እና የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ማቅረብ፤

## ርዕይ

በሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች እና በቀጠናዊ የሰላም፣ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰዋዊ እና ቁሳዊ ልማት ላይ፣ በኢጋድ ቀጠና ተቀዳሚ የምርምር እና ፖሊሲ አመንጪ ማዕከል መሆን፤

## መሠረታዊ ዕሴቶች

- አጽንዖተ ትኩረት፡- ከፍተኛ ትኩረት የተሰሩ እና ተጨባጭነት ያላቸው ጥናት ምርምሮችን ማቅረብ።
- አዲስነት፡- ለዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ተግዳሮቶች ፈጠራዊ እና ተለዋዋጭ መፍትሔዎች የታከለባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ማዋጣት
- ታማኝነት፡- ተዓማኒነት ያላቸውን የምርምር ውጤቶችን በማቅረብ ተዓማኒነትን መጠበቅ

## ግቦች

ኢትዮጵያ እና በኢጋድ ቀጠና የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል ፓርላማዎች በሚከተሉት መንገዶች ማጠናከር

- ተጨባጭ ምርምሮችን መከወን
- የእንደራሴዎችን ብቃት ለማሳደግ የዐቅም ግንባታ ድጋፎችን ማድረግ
- ተጠያቂነትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ክንውኖችን መከታተል

+251 99 808 5013

+251 115 57 74 96

info@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

UNECA, SA Building, 9th Floor,

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.

# ማውጫ


**የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወርኃ ግንቦት ክራሞት** ........ 1

**በወሩ የተካሄዱ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባዎች** ........ 2

**1. የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት** ........ 3

1.1 የጸደቁ ሕግጋት ........ 3

1.2 ረቂቅ ሕግጋት ........ 5

1.3 አሥረጂ መድረኮች ........ 7

**2. የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር** ........ 11

2.1 የተቋማት ሪፖርቶች ........ 12

2.2 የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶች ........ 19

**3. የፓርላማው ዲፕሎማሲ** ........ 21

**4. እንደራሴዎቹ ስለ'ራሳቸው በ'ራሳቸው** ........ 25

**5. ኢትዮጵያ ምን ተስማማች?** ........ 27

**6. የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታ፦ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የንግድ ፖሊሲ ዙሪያ** ........ 28

6.1 ስለ ፖሊሲው ከተነገሩት ........ 29

6.2 ፖሊሲው ምን ይዟል? ........ 31

6.3 ክርክሮቹ እና ተግዳሮቶቹ ........ 33

6.4 የብሪጅ ምክረ-ሐሳቦች ........ 36

6.5 ምክረ-ሐሳቦች ለሕዝብ ተወካዮቹ ........ 36


# የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወርኃ ግንቦት ክራሞት

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ወርኃ ግንቦትን ያጠናቀቀው፣ ተለምዷዊዎቹን ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነቶቹ የሆኑትን ሕግጋት ማውጣት፣ ሥራ አሥፈጻሚ ተቋማትን መቆጣጠር እና የአሥረጂ መድረኮችን ከማካሄድ ባለፈ፣ የተወሰኑ የተቋማት ጉብኝቶችን እና ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲዎችንም ከውኗል። ይኽች የግንቦት የእንደራሴ ዕትምም፣ እነኚን ርዕሰ-ጉዳዮች እና ለወሩ መገባደጃ ይሆናል ብላ የመረጠችውን ዳሰሳዊ ምልከታዋን አካታ እንዲኽ ተዘጋጅታለች።

## በወሩ የተካሄዱ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባዎች

| 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን | ቀን | አጀንዳዎች |
|---|---|---|
| 20ኛ መደበኛ ስብሰባ | ግንቦት 4 | * የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር መቅደስ ዳባ፣ ከእንደራሴዎቹ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች በቃል የሚሰጡትን ምላሽ ማድመጥ፤ |
| 21ኛ መደበኛ ስብሰባ | ግንቦት 6 | * የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጅን መርምሮ ማጽደቅ፤ |
| 22ኛ መደበኛ ስብሰባ | ግንቦት 11 | * የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርን የ2018 በጀት ዓመት የ9 ወራት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ማድመጥ፤ |
| 23ኛ መደበኛ ስብሰባ | ግንቦት 27 | * በኢትዮጵያ እና በአፍሪካ ልማት ባንክ፣ በኢትዮጵያ እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረጉ የብድር ስምምነቶች መርምሮ ማጽደቅ፤<br>* በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በሴራሊዮን ሪፐብሊክ መንግስታት፣ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በአንጎላ ሪፐብሊክ መንግስታት፣ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በባንግላዲሽ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ መንግስታት፣ እንዲኹም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በኢስዋቲኒ ንጉሠ ነገሥት መንግስታት መካከል የተፈረመውን የኹለትዮሽ የአየር አገልግሎት ስምምነት ረቂቅ ዐዋጅ መርምሮ ማጽደቅ፤<br>* በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግስት እና በሩሲያ ፌዴሬሽን መካከል የጋራ የባዮሎጂ ምርምር ማዕከል ለማቋቋም የተፈረመውን ስምምነት ረቂቅ ዐዋጅ መርምሮ ማጽደቅ፤<br>* በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በቬትናም ሶሻሊስት ሪፐብሊክ መንግስታት መካከል የዲፕሎማቲክ ወይም ኦፊሻል የአገልግሎት ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተፈረመ ስምምነት ረቂቅ ዐዋጅን መርምሮ ማጽደቅ፤ እና፣<br>* የፌዴራል ታክስ አሥተዳደር ማሻሻያ፣ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ፣ የምግብ ሥርዓት እና ሥርዓተ ምግብ፣ የኢትዮጵያ የካርበን እና የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ ረቂቅ ዐዋጆችን መርምሮ ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች መምራት፤ |

# 1. የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ በዚኽ ግንቦት ወር፣ **አንድ ረቂቅ ዐዋጅን እና ኢትዮጵያ ከተለያዩ አገራት ጋር የተስማማቻቸውን ስምምነቶች ሲያጸድቁ፤ አምስት ረቂቅ ዐዋጆችንም** ይመለከታቸዋል ወዳሏቸው ቋሚ ኮሚቴዎች መርተዋቸዋል።

## 1.1 የጸደቁ ሕግጋት

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ በወርኀ ግንቦት ካካሄዷቸው መደበኛ ስብሰባዎች መካከል፣ በ21ኛው መደበኛ ስብሰባቸው፣ **የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጅን** አጽደቀዋል። የረቂቀ ዐዋጁን ሪፖርት እና የውሳኔ ሐሳብ ለአንደራሴዎቹ ያቀረቡት፣ በምክር ቤቱ የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ሰለሞን ላሌ፣ ማሻሻያ ዐዋጁ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከፋይናንስ ተቋማት ጋር ያላቸውን ትስስር በማጠናከር እና የፋይናንስ አቅርቦት ችግራቸውን በመፍታት ተወዳዳሪነታቸውን ከማሳደግ ባሻገር፣ ጠንካራ የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ከብክነት እና ምዝበራ በመታደግ ረገድ ሚናው የጎላ መሆኑን አብራርተዋል።

ሰብሳቢው አክለውም፣ በተበታተነ ኹኔታ ተደራጅተው የሚገኙ ማኅበራት ሰብሰብ ብለው እንዲደራጁ እና ትርፋማ እንዲሆኑ ለማስቻል እንዲኹም ጠንካራ የውስጥ አመራር እና የአሥተዳደር ሥርዓትን ለመዘርጋት እንደሚያግዝ ገልፀዋል ተብሏል። የተከበሩ ሰለሞን፣ በማኅበራት ውስጥ የሴቶችን የአመራርነት ተሳትፎ በተመለከተ ቁጥራቸው የሚፈቅድ አባል ሴቶች በሚገኙባቸው ማኅበራት ላይ ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑንም ጠቁመዋል። በመጨረሻም ምክር ቤቱ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጁን፣ ዐዋጅ ቁጥር 1416/2018 አድርጎ በሙሉ ድምፅ አፅድቆታል።



*የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ሰለሞን ላሌ፣ በዐዋጁ መጽደቅ ወቅት፤*

በዚኹ ወርኀ ግንቦት መገባደጃ ላይ የተካሄደው 23ኛው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ፣ **ኢትዮጵያ ከተለያዩ አገራት ጋር የተሰማማቻቸውን ስምምነቶችም** መርምሮ ማጽደቁን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ይጠቁማል። ከዚኽ አኳያም ምክር ቤቱ በቀዳሚነት ያጸደቀው፣ **በኢትዮጵያ መንግስት እና በሩሲያ ፌዴሬሽን መካከል የጋራ የባዮሎጂ ምርምር ማዕከል ለማቋቋም የቀረበ ረቂቅ ዐዋጅን**

ሲሆን፤ የረቂቁን የውሳኔ ሐሳብ ያቀረቡትም፣ በምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማሕዲ መሆናቸውን ተጠቅሷል።

በኢትዮጵያ እና በሩሲያ መካከል የጋራ ባዮሎጂካል ምርምር ማዕከል ለማቋቋም የተፈረመው ስምምነት በአገራቱ መካከል የጋራ ሳይንሳዊ እና ጥናታዊ የምርምር ሥራዎችን ለማሳደግ እንደሚያግዝ የተናገሩት ምክትል ሰብሳቢው፣ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ እድገትን ለማፋጠን የዓሳ ሀብት ልማት ከፍተኛ ፋይዳ ያለው እንደመሆኑ፣ ኢትዮጵያ ከራሷ አልፎ ወደ ውጭ ምርቱን ለመላክ ሩሲያ በዘርፉ ካላት ከፍተኛ ልምድ ለማካበት ረቂቁ እንደሚያግዝም ጠቅሰዋል ተብሏል። የሕዝብ ተወካዮቹም፣ ይኸንኑ ረቂቅ ዐዋጅ፣ዐዋጅ ቁጥር 1421/2018 ሲሉ በሙሉ ድምፅ አጽድቀውታል።

በዚኹ 23ኛው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ ላይ የጸደቀው ሌላኛው የስምምነት ረቂቅ፣ **በኢትዮጵያ እና በቬትናም መንግስታት መካከል** የዲፕሎማቲክ ወይም ኦፊሻል የአገልግሎት ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተፈረመው ስምምነት ነበር። ይኸንንም ረቂቅ ለምክር ቤቱ ያቀረቡት የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማሕዲ ሲሆኑ፤ ስምምነቱ በአገራቱ መካከል እያደገ የመጣውን የኹለትዮሽ ትብብርን እና የዲፕሎማሲ ግንኙነት መስመርን ለማጠናከር የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ የሚፈጥር መሆኑን አስረድተዋል።

ከዚያ ባለፈም፣ ቪዛ ለማግኘት የሚያስፈልጉትን ቅድመ-ኹኔታዎች እና የሚወስደውን ጊዜ በማስቀረት የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት የያዙ የኹለቱ አገራት ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት እና ዲፕሎማቶች እንዲኹም ዜጎች በየጊዜው የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በቀላሉ እንዲመቻች የሚያደርግ መሆኑን አያይዘው ተናግረዋል ተብሏል። በመጨረሻም እንደራሴዎቹ ረቂቅ ዐዋጁን፣ ዐዋጅ ቁጥር 1422/2018 አድርገው በሙሉ ድምፅ አጽድቀውታል።

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላቱ፣ በዚያው በዕለተ ኅሙስ በዋለው 23ኛ መደበኛ ስብሰባቸው፣ ኢትዮጵያ **ከተለያዩ አገራት ጋር ያደረገቻቸውን የአየር አገልግሎት ስምምነት ረቂቅ ዐዋጆችንም** አጽድቀዋል። የረቂቅ ዐዋጆቹን የውሳኔ ሐሳቦች ያቀርቡትም፣ የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማሕዲ ሲሆኑ፤ የአየር አገልግሎት ስምምነት ረቂቅ ዐዋጆቹ የውጭ መዋዕለ-ንዋይን በመሳብ እና የአየር ትራንስፖርት መዳረሻዎችን በማስፋት፣ ለአገሪቷ የአየር ትራንስፖርት እና ምጣኔ-ሀብታዊ ዕድገት ያላቸው ሚና ወሳኝ መሆኑን ለእንደራሴዎቹ አስረድተዋቸዋል ተብሏል።

ከእነዚኽ ስምምነቶች መካከል **በኢትዮጵያ እና በሴራሊዮን ሪፐብሊክ መንግስት** በኩል የተፈረመው አንዱ ሲሆን፤ ስምምነቱም፣ ለአየር መንገዶች ወደ ተመረጡ መዳረሻዎች በቀጥታ ለማረፍ እና ምቹ የአቪዬሽን አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል መሆኑ

ተገልጿል። ስምምነቱም፣ ዐዋጅ ቁጥር 1417 /2018 ሆኖ በሙሉ ድምጽ ጸድቋል።

ሌላይኛው ስምምነት፣ **በአንጎላ ሪፐብሊክ እና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል** የተፈረመው ሲሆን፣ ምክር ቤቱም ይኽንኑ ረቂቅ፣ ዐዋጅ ቁጥር 1418 /2018 አድርጎ በሙሉ ድምጽ ማጽደቁ ተዘግቧል። የውጪ ቀጥተኛ መዋዕለ-ንዋይን ለመሳብ፣ በንግድ እና በቱሪዝም እንዲኹም የውጪ ምንዛሬ በማስገኘት ረገድ ጉልህ ሚና ይኖረዋል የተባለውን፣ **በኢትዮጵያ እና በባንግላዲሽ መንግስታት መካከል** የተደረገው የአየር አገልግሎት ስምምነት ረቂቅም፣ የምክር ቤቱ አባላት ዐዋጅ ቁጥር 1419/ 2018 አድርጎ በሙሉ ድምጽ ይጸድቅ ዘንድ ፍቃዳቸው ሆኗል።

ሌላው በዚያው መደበኛ ስብሰባ በምክር ቤቱ የጸደቀው የአየር አገልግሎት ረቂቅ ዐዋጅ፣ **በኢትዮጵያ እና በኢስዋቲኒ መንግስታት መካከል** የተደረገው ስምምነት ሲሆን፤ ያለ በረራ ድግምግሞሽ ገደብ የጭነት በረራዎችን ማከናወን ጨምሮ ለበረራ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስገባትን የሚያካትት በመሆኑ የበረራ ወጪን እንደሚቀንስ የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማሕዲ የረቂቁን የውሳኔ ሐሳብ ሲያቀርቡ መናገራቸው ተጠቅሷል። የምክር ቤቱ አባላትም፣ ረቂቁን ዐዋጅ ቁጥር 1420/ 2018 አድርገው በሙሉ ድምጽ ማጽደቃቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ያሳያል።



*የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማሕዲ፣ ረቂቅ ስምምነቶቹን ባቀረቡበት ወቅት፤*

## 1.2 ረቂቅ ሕግጋት

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ በ23ኛው መደበኛ ስብሰባቸው ይመለከታቸዋል ወዳሏቸው ቋሚ ኮሚቴዎች ከመሯቸው ረቂቅ ዐዋጆች መካከል ቀዳሚው፣ **የፌዴራል ታክስ አሥተዳደር ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጅን** ሲሆን፤ ለዝርዝር ዕይታ የመሩትም በምክር ቤቱ ለፕላን በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ነበር።

በረቂቁ ዙሪያ ለምክር ቤቱ ማብራሪያ የሰጡት፣ በምክር ቤቱ የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚኒስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ ሲሆኑ፤ 'ርሳቸውም፣ ረቂቅ ዐዋጁ የታክስ አሥተዳደር ሥርዓትን በማዘመን፣ በታክስ ከፋዩ ዘንድ የሚነሱ መሠረታዊ የፍትሓዊነት እና የመልካም አሥተዳደር ቅሬታዎችን በዘላቂነት መፍታት የሚያስችል እንደሆነ ገልጸዋል።

ረቂቅ ዐዋጁ፣ በአገሪቷ የታክስ አሥተዳደር ሥርዓት ውስጥ ተጠያቂነትን፣ ቅልጥፍናን፣ ፍትሐዊነትን እና ግልፅነትን ለማስፍን የታክስ ሕግጋትን በተጠናከረ መልኩ ለማስፈጸም እንዲኹም፣ በታክስ ከፋዩ እና ሰብሳቢው መካከል ያለውን ግንኙነት በሕግ የበላይነት ላይ እንዲመሰረት የሚያስችሉ ቁልፍ ድንጋጌዎችን የያዘ እንደሆነ የመንግስት ተጠሪው ማብራራታቸው ተጠቅሷል። የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ አክለውም፣ የመንግስትን የገቢ አሰባሰብ አቅም በታማኝነት ላይ ተመሰርቶ ለማጠናከር ከፍተኛ ፋይዳ ያለው የሕግ ማዕቀፍ መሆኑንም ማብራራታቸው ተዘግቧል።

የሕዝብ ተወካዮቹ በዚያው መደበኛ ስብሰባቸው የተመለከቱት ሌላይኛው ረቂቅ ዐዋጅ፣ **የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ረቂቅ ዐዋጅን** ሲሆን፤ ዐዋጁንም በምክር ቤቱ ለግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ለዝርዝር ዕይታ መርተውታል። ይኽንንም ረቂቅ አስመልክቶ ለምክር ቤቱ ማብራሪያ የሰጡት የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ እንደነበሩ ሲጠቀስ፤ የመንግስት ተጠሪውም፣ የግብርና አሰራሮች በማላቅ ወደ ዘመናዊ፣ ተወዳዳሪ እና የገበያ መር ሥርዓት መሸጋገር አስፈላጊ በመሆኑ የኢትዮጵያን ግብርና ዘመናዊ በማድረግ ረገድ ረቂቅ ዐዋጁ አስፈላጊ እንደሆነ ገልፀዋል ተብሏል።

ሚኒስትሩ አክለውም፣ አነስተኛ ይዞታ ያሏቸውን አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮችን በግብርና ቢዝነስ ኩባንያ በማደረጃት ምርታማነትን በማጎልበት የምርት ጥራትን ለማሳደግ፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና ኹሉን ዓቀፍ የምጣኔ ሀብት እድገትን ለማስፈን ረቂቅ ዐዋጁ ወሳኝ ሚና እንዳለው ማተታቸውን ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ያሳያል።

ግንቦት 23 ቀን 2018 ዓ.ም. በዋለው ይኸው 23ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ፣ የሕዝብ ተወካዮቹ ሊመለከቱት የፈቀዱት ሦሥተኛው የወሩ ረቂቅ ዐዋጅ፣ **የምግብ ሥርዓት እና ሥርዓተ-ምግብ ረቂቅ ዐዋጅ** የተሰኘው ሲሆን፤ ይኽንን ረቂቅ ዐዋጅም፣ በምክር ቤቱ ለጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ለዝርዝር ዕይታ መምራታቸው ተጠቅሷል። በዚኽ ረቂቅ ዐዋጅ ዙሪያም፣ ማብራሪያ ያቀረቡት በምክር ቤቱ የመንግስት ተጠሪው የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ ሲሆኑ፤ መንግስት የምግብ እና ሥርዓተ-ምግብ ዋስትና ለአገሪቱ እድገት ጉልህ ሚና ይጫወታል ብሎ እንደሚያምን መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።

የተስተካከለ እና የተመጣጠነ ምግብ ያገኘ ትውልድ መፍጠር ይቻል ዘንድ፣ አኹን ያለውን እና የወደፊቱን ምጣኔ ሀብት እድገት ለማስቀጠል፣ እንዲኹም የአገሪቱን የምግብ ሥርዓት እና ሥርዓተ-ምግብ ለማረጋገጥ የሚያግዝ ረቂቅ ዐዋጅ እንደሆነም ሚኒስትሩ ጨምረው ገልፀዋል።

ከላይ በጠቀስነው የዕለቱ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ፣ እንደራሴዎቹ ወደ ፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የመሩት ረቂቅ ዐዋጅ፣ ኢትዮጵያ ዘመናዊ፣ ጠንካራ እና ሕጋዊ መሠረት ያለው የስታቲስቲክስ ማዕቀፍ እንዲኖራት የሚያስችል የተባለውን ረቂቅ

ዐዋጅ መሆኑን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷል። ረቂቁን ለምክር ቤቱ አባላት ያብራሩት የመንግስት ተጠሪው የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ፣ ረቂቅ ዐዋጁ ሙያዊ ነፃነትን በማረጋገጥ እና የተቆጣጣሪ እና የፈጻሚ ሚናዎችን በመለየት የተሻሻሉ የማስተባበር ዘዴዎችን መደበኛ አሰራር በማድረግ የስታቲስቲክስ ተዓማኒነት ጥራት ላይ፣ እንዲኹም አገሪቱ ቅድሚያ በምትሰጣቸው የልማት አቅጣጫዎችን ትኩረት በማድረግ፣ የአገሪቱን እድገት ለማፋጠን የራሱ ሚና እንዳለው አስረድተዋል ተብሏል።

ከዚኽ ባለፈም፣ ረቂቁ ለአገራዊ ዕቅድ እና ለውሳኔ ሐሳብ የሚውሉ ጥራታቸው የተረጋገጠ እና ወቅቱን የጠበቀ የስታቲስቲክስ መረጃ እንዲሰበሰቡ፣ እንዲጠናቀሩ፣ እንዲተነተኑ እና እንዲሰራጩ የሚያስችል ሥርዓት እንዲኖር ረቂቅ ዐዋጁ ያግዛል ሲሉም ሚኒስትሩ መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ በዚኹ ወርኃ ግንቦት የተመለከቱት የመጨረሻው ረቂቅ ዐዋጅ፣ **የኢትዮጵያ ካርበን ገበያ ረቂቅ ዐዋጅን** ሲሆን፤ ይኽንን ረቂቅ ዐዋጅም አስመልክቶም ለእንደራሴዎቹ ማብራሪያ የሰጡት የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ፣ ረቂቅ ዐዋጁ የካርቦን ግብይት አጠቃላይ አሰራሮችን እና ሂደቶችን በግልፅ በመደንገግ፣ ዘርፉ በሥርዓት እና የአገራችንን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲመራ ኃላፊነትን እና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን መሆኑን ተናግረዋል ተብሏል።

ሚኒስትሩ ለጥቀውም፣ በካርበን ገበያው የፋይናንስ ገቢያችንን ከማሳደግም ባሻገር ብሔራዊ ጥቅማችንን በማስጠበቅ ረገድ የራሱ ሚና እንዳለው መናገራቸውን ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ጠቁሟል። ምክር ቤቱ፣ ረቂቅ ዐዋጁን ለፕላን በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ለዝርዝር ዕይታ መርቶታል ተብሏል።



***በምክር ቤቱ የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚኒስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ፣ ረቂቅ ዐዋጆቹን ለምክር ቤቱ ባቀረቡበት ወቅት፤***

## 1.3 አሥረጂ መድረኮች

በወርኃ ግንቦት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቱ ከተካሄዱት የአሥረጂ መድረኮች መካከል በጊዜ ምጣኔ ቀዳሚው፣ **የመረጃ ነጻነት ረቂቅ ዐዋጅን** የተመለከተው ነበር። መድረኩን ያዘጋጀው፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን፣ የኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ እውነቱ

አለኑ፣ የመረጃ ነጻነት ረቂቅ ዐዋጅ ዜጎች በመረጃ ላይ ተነስተው ጥቅሞቻቸውን እንዲያስከበሩ ሆኖ የተዘጋጀ ነው ብለዋል ተብሏል።

የተከበሩ እውነቱ አያይዘውም፣ ከባለድርሻ አካላት የተነሱ ገንቢ ሐሳቦች ዐዋጁን ለማዳበር ጠቃሚ መሆናቸውን ጠቁመው፣ ረቂቅ ዐዋጁ እስከሚጸድቅ ድረስም ከተለያዩ አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ዐዋጁ ዳብሮ እንዲወጣ ጥረት የሚደረግ መሆኑን መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ አዝመራ አንደሞ በበኩላቸው፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በተደረጉት ውይይቶች ረቂቅ ዐዋጁን ለማዳበር ጠቃሚ ሐሳቦች በመገኘታቸው፣ ሕዝቡ ትክክለኛ መረጃ አግኝቶ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚረዳ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ዋና ዕንባ ጠባቂ ወይዘሮ ስመኝ ውቤ በበኩላቸው፣ ከባለድርሻ አካላት የተነሱ አንዳንድ አስተያየቶች ረቂቅ ዐዋጁን ለማዳበር ጠቃሚ ቢሆኑም፣ ከመዘጋጀቱ በፊት ጥናት ተደርጎ እና ባለፉት ዓመታት ያጋጠሙትን የአፈጻጸም ችግሮች መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ ረቂቅ ዐዋጅ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ወይዘሮ ስመኝ አክለውም፣ ረቂቅ ዐዋጁ ከተዘጋጀ በኋላ ከተለያዩ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎ አንዳንድ ሐሳቦች የተካተቱ ቢሆንም፣ የመረጃ ነጻነት ዐዋጅ ዳብሮ ቢወጣ ሕዝብን ተጠቃሚ ስለሚያደርግ አንዳንድ ሐሳቦችን እንደገና ለማየት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል ተብሏል።



*የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ዋና ዕንባ ጠባቂዋ ወይዘሮ ስመኝ ውቤ፣ በአሥረጂ መድረኩ ወቅት፤*

የወሩ ኧለተኛው የአሥረጂ መድረክ፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ **ከተለያዩ አገሮች ጋር በተደረጉ የአየር አገልግሎት ስምምነት ረቂቅ ዐዋጆች ዙሪያ** ያካሄደው እንደነበር የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቅሳል። ቋሚ ኮሚቴው በአራት የአየር አገልግሎት ስምምነት ረቂቅ ዐዋጆች ላይ ውይይት ያደረገ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ **ባንግላዲሽ፣ አንጎላ፣ ኢስዋቲኒ እና ሴራሊዮን** በሚያደርጋቸው በረራዎች የተፈረሙ የኹለትዮሽ የአየር አገልግሎት ስምምነቶች መሆናቸውም ተገልጧል።

ቋሚ ኮሚቴው ከነዚኽ አገራት ጋር የተደረጉት ስምምነቶች፣ ከኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት እና ከሌሎች ሕግጋት፣ እንዲኹም ኢትዮጵያ ካፀደቀቻቸው ዓለም

ዓቀፍ ድንጋጌዎች ጋር የሚጋጭ እንዳይሆን የተለየ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ መግለጹም ተጠቅሷል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፣ ረቂቅ ዐዋጆቹን በተመለከተ ቋሚ ኮሚቴው የውሳኔ ሐሳብ እንደሚሰጥ ገልጸው፣ ስምምነቶቹ የአገራትን ሉዓላዊነት ባከበረ መልኩ የኢትዮጵያን ደኅንነት በማስጠበቅ እንዲኹም ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትን በማጠናከር ኢትዮጵያ ተጠቃሚ እንድትሆን ረቂቅ ዐዋጆቹን ማዳበር እንደሚያስፈልግም አስገንዝበዋል።



***የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፣ በአሥረጂ መድረኩ ወቅት፤***

የወሩ ሦሥተኛ የአሥረጂዎች መድረክ የነበረው፣ **በጉምሩክ ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጅ** ዙሪያ የተከወነው ሲሆን፣ መድረኩን የመራው በምክር ቤቱ የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መሆኑ ተጠቅሷል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ፣ በተለያዩ መድረኮች በዐዋጁ ላይ ሰፊ ግብዓት መሰብሰብ መቻሉን ገልፀው፣ የዐዋጁ አስፈላጊነት እንዲሁም መሻጋሪያ ድንጋጌ ያልተካተተበትን አልፎም፣ የወደብ ቆይታን በተመለከተ በየብስ 45 ቀን፣ በአየር 30 ቀን በሚል የተቀመጠው የሥራ ቀናት ተብሎ በግልፅ ማስቀመጥ ያልተቻለበት ምክንያት አስመልክቶ ማብራሪያ እንዲሰጥ ጠይቀዋል።

ሰብሳቢው አያይዘውም ኮንትሮባንድ የጫነ ተሽከርካሪን ከመውረስ ይልቅ ቅጣቱን ከፍ ማድረግ የተሻለ እንደሆነ እና የውርስ ሂደቱም በመመሪያ ሳይሆን በደንብ እንደሚወሰን ተደርጎ መቀመጥ እንዳለበት ጠቁመው፣ አሥተዳደራዊ ቅጣቶችን በዐዋጁ ማካተት እንደሚገባም አስገንዝበዋል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው አባል የተከበሩ ደበበ አድማሱ በተራቸው፣ የባህር ትራንዚት እና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያ ያልከፈሉ ባለንብረቶች ንብረታቸው ተሸጦ የአገልግሎት ክፍያ እንደሚከፈል በዐዋጅ የተደነገገ መሆኑን ተቋሙ በጹሑፍ የገለፀ በመሆኑ፣ ከዚህ ዐዋጅ ጋር ተናባቢ ማድረግ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የጉምሩክ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አዘዘው ጫኔ በበኩላቸው፣ የወደብ ቆይታን በተመለከተ የሥራ ቀናት በሚል ማስተካከል የሚቻል መሆኑን ተናግረዋል ተብሏል። ኮንትሮባንድ የጫነ ተሽከርካሪ ውርስን በተመለከተ ሆን ብለው ከተሽከርካሪው አካል ወጪ የእቃ መደበቂያ ሰርተው ኮንትሮባንድ የሚጭኑ መኖራቸውን ያነሱት ኮሚሽነሩ፣ ቅጣቱን ከፍ ማድረጉ ተጨባጭ ለውጥ የሚያመጣ ባለመሆኑ የባለንብረቱ ተሳትፎ የሌለበት መሆኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ

ተሸከርካሪው ለባለንብረቱ የሚመለስበት አግባብ መኖሩን አስረድተዋል።

ከኮንትሮባንድ ውርስ የሚገኝ ገቢን በተመለከተ ኮንትሮባንድ ንግድን በመከላከል ሥራ ላይ ሚና ያላቸው አካላትን አቅም ለመገንባት እንደሚውል ተደርጎ የሚስተካካልበት አግባብ እንደሚኖርም ኮሚሽነር አዘዘው ጨምረው መናገራቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ጠቅሷል።



***የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ፣ በአሥረጂ መድረኩ ወቅት፤***

በምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ **በኢትዮጵያ መንግስት እና በሩሲያ ፌዴሬሽን መካከል የጋራ የባዮሎጂ ምርምር ማዕከል ለማቋቋም** በተፈረመው ረቂቅ ዐዋጅ ዙሪያ ከተለያዩ ተቋማት ከተውጣጡ ባለድርሻ አካላት ጋር ያካሄደው መድረክ ደግሞ፣ የወሩ የመጨረሻ የአሥረጂዎች መድረክ ሆኗል። ስምምነቱ ኢትዮጵያ በሳይንሳዊ ጥናት እና በባዮሎጂካል ምርምር ዘርፍ የምታደርገውን እንቅስቃሴ የሚደግፍ በመሆኑ፣ በምክር ቤቱ ጸድቆ ወደ ሥራ እንዲገባ እንደሚደረግ የተናገሩት ደግሞ፣ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ ነበሩ።

ሰብሳቢው አክለውም፣ ሚዛናዊ እና ውጤታማ የሕግ አተገባባር እንዲኖር ለማስቻል በረቂቅ ስምምነት ዐዋጁ ላይ ቋሚ ኮሚቴው በርካታ አካላትን በማወያየት ላይ እንደሚገኝም ተናግረዋል ተብሏል። ከቋሚ ኮሚቴው ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ እና ማብራሪያ የሰጡት በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚኒስትሩ አማካሪ ሰሎሞን በላይ፣ ስምምነቱ ለ35 ዓመታት በባዮሎጂካል የምርምር ዘርፍ በፕሮጀክት ደረጃ ሲተገበሩ የቆዩ እንቅስቃሴዎችን ወደ ተቋም ለመሳደግ የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል፡፡



***የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው አባላት በአሥረጂ መድረኩ ወቅት፤***

የሚኒስትሩ አማካሪ ለጥቀውም፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምርምር መሰረተ-ልማት ግንባታ እና በጥናት እና ምርምር የሚገኙ ውጤቶችን ቅርጽ በማስያዝ የአገራቱን ብሔራዊ ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ ተጠቃሚ

እንዲሆኑ ለማስቻል ስምምነቱ በትኩረት ሲታይ መቆየቱን ለቋሚ ኮሚቴው አስረድተዋል ተብሏል።

## 2. የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በወርኃ ግንቦት የዐራት ተቋማትን የ2018 ዓ.ም. የበጀት ክንውንን እና የተቋማቱን የ2019 በጀት ፍላጎት ሲገመግም፣ የኹለት ተቋማትን የዘጠኝ ወራት የዕቅድ አፈጻጸምም አድምጦ፣ የጤና ሚኒስትር ሚኒስትሯን ምላሽ እና ማብራሪያም ማድመጡም አንዱ ክንውኑ ነበር።

### 2.1 የተቋማት ሪፖርቶች

ምክር ቤቱ በወሩ ከተመለከታቸው ተቋማት መካከል በጊዜ ምጣኔ በቀዳሚነት፣ በምክር ቤቱ የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ **የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን** የ2018 በጀት ዓመት የ9 ወራት የበጀት አፈጻጸም ሪፖርት እና የ2019 በጀት ዓመት የበጀት ፍላጎትን አስመልክቶ ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች ጋር ውይይት ማድርጉ የሚጠቀስ ክንውኑ ነበር። የቋሚ ከሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄም፣ ተቋሙ አገልግሎቱን ለማዘመን እያከናወናቸው ያሉ ተግባራት አበረታች መሆናቸውን እንዲኹም የተሻለ የበጀት አጠቃቀም መኖሩን ጠቀመው፣ የሕንፃ ጥገናን በተመለከተ በቂ ጥናት ተደርጎ እና የካፒታል በጀት ተይዞለት በዘላቂነት መጠገን እንደሚገባ ገልፀዋል ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው አባል የተከበሩ ዶ.ር. አለሙ ጀንበሩ፣ የ2019 በጀት ዓመት የበጀት ፍላጎት በዝርዝር ማቅረብ መቻሉ፣ የፋይናንሺያል አፈጻጸሙ 87. 8 በመቶ መሆኑ፣ የፊዚካል አፈጻጸሙ ያለበት ደረጃ የተሻለ መሆኑን እንዲኹም የቀረቡት የ2019 በጀት ዓመት የበጀት ጥያቄዎች ከፍ ያሉበትን ምክንያት በዝርዝር ማቅረብ መቻሉ በጥንካሬ የሚወሰዱ መሆናቸውን መጥቀሳቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ጠቅሷቸዋል።



***የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ቴድሮስ ምህረት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቷ ሌሊሴ ደሳለኝ እና ባልደረቦቻቸው በመድረኩ ላይ በተገኙበት ወቅት፤***

የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቷ ሌሊሴ ደሳለኝ በበኩላቸው፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በ2018 በጀት ዓመት የተመደበለትን የጥገና በጀት በአግባቡ መጠቀሙን ገልጸው፣ በዚኽ ዓመት የተጠየቁ የጥገና ወጪዎች ከፍ እንዲሉ ያደረገው የጥገና ግብዓት እና ማሽነሪዎች ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት እንደሆነ አንስተዋል። ዘጠኝ የበጀት ርዕሶችን በመለየት ከፍ ያለ በጀት መጠየቁን የጠቆሙት ፕሬዝደንቷ፣ እነዚኽ የመደብ ርዕሶች የግዴታ ወጪዎችን፣ ነዳጅን እና የሕንፃ ጥገና

ወጪዎችን ያካተተ መሆኑን መናገራችውን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ጠቅሷቸዋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ **የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን** የ2018 የበጀት አፈጻጸም እና የ2019 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ዕቅድ ላይ ከቦርዱ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ያደረገው ውይይትም እንዲኹ የሚጠቅሰው የወሩ የምክር ቤቱ የሥራ ተቋማት ቁጥጥር ክንውኑ ነበር። ቋሚ ኮሚቴው የቦርዱን የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈጻጸም መነሻ በማድረግ በአቀራረብ ረገድ የታዩ ክፍተቶች እንዲኹም በመደበኛው እና በምርጫ ማስፈጸሚያ በጀት መካከል ግልጽ ልዩነት እንዲኖር እና የካፒታል በጀት አጠቃቀም ለምክር ቤቱ ቤቱ ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲቀርብ የሚሉ አስተያየቶቹንም ለቦርዱ ኃላፊዎች ማቅረቡን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ጠቅሷል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ እንደገለጹት፣ ቦርዱ የሚያካሄዳቸውን ምርጫዎች በራሱ የበጀት አቅም እንዲፈጽም መደገፍ እና የውጭ ጣልቃ ገብነትን ማስቀረት የምክር ቤቱ ቀዳሚ ተግባር ነው ብለዋልም ተብሏል። ቋሚ ኮሚቴው ቦርዱ የሚሰራቸውን ሥራዎች ያለምንም መስተጓጎል እንዲፈጽም እና የሚያስፈልገውን በጀት እንዲያገኝ ለማስቻል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ለመስራት ቁርጠኛ መሆኑን የጠቀሱት ሰብሳቢው፣ የአዳዲስ ቅርንጫፎች የሰው ኃይል ቅጥር እና ሌሎች ሥራዎች በታቀደላቸው ደረጃ እንዲከናወኑ እና ቦርዱን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ በትብብር እንደሚሠራ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢዋ ወ/ሮ ሜላትወርቅ ኃይሉ በበኩላቸው፣ ቦርዱ ካለበት ከፍተኛ የሥራ ጫና አንጻር እያስመዘገበ ያለውን ስኬት ያስረዱ ሲሆን፣ የበጀት አፈጻጸሙም አኹን ላይ 90 በመቶ መድረሱን ጠቅሰው፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የምርጫ አሥፈጻሚዎችን በማሰማራት፣ የምርጫ ቁሳቁሶችን በማጓጓዝ፣ እንዲኹም ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚገባውን ድጋፍ በማመቻቸት ቦርዱ ለዲሞክራሲያዊ ሂደቱ ስኬት በትኩረት እየሰራ መሆኑን አስገንዝበዋል ተብሏል።



***የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢዋ ወ/ሮ ሜላትወርቅ ኃይሉ፣ በመድረኩ ላይ በተገኙበት ወቅት፤***

ይኸው የየፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ **የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ)** ያቀረበውን የ2019 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ዕቅድ ፍላጎትም፣ በዚኹ ግንቦት ወር መገምገሙ ተዘግቧል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ

የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄም፣ መንግስት የዜጎችን ሰብዓዊ መብት ለማስከበር ላለው ቁርጠኝነት ማሳያ ባለፉት ዓመታት ለኮሚሽኑ የሚመደበው በጀት በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጨምር ማድረጉን ገልጸዋል።

ተቋሙ ብሔራዊ ጥቅምን እና ገለልተኝነቱን በአግባቡ አስጠብቆ እንዲቀጥል ምክር ቤቱ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ የገለጹት ሰብሳቢው፣ ኮሚሽኑ ያቀረባቸው የበጀት ፍላጎቶች እና የመሠረተ-ልማት ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኙ በትኩረት እንደሚሰራ አረጋግጠዋል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም አለማየሁ በበኩላቸው፣ እንደ ሕዝባዊ ጉባኤ ያሉ የአንድ ጊዜ ወጪዎችን ከመደበኛ በጀት ነጥሎ በፕሮጀክት መልክ ማቅረብ እንደሚገባ እና ሌሎች የበጀት ጥያቄዎችንም በተጨባጭ ቁጥር ደግፎ ማምጣት ለመንግስት ውሳኔ አሰጣጥ ወሳኝ መሆኑን አስገንዝበዋል።

የኢሰመኮ ዋና ኮሚሽነር ብርሃኑ አዴሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽ እና ማብራሪያ፣ የበጀት ጭማሪው አስፈላጊ የሆነባቸውን መሠረታዊ ምክንያቶች በዝርዝር ከማቅረባቸው ባለፈ፣ ውይይቱ በአጠቃላይ የኮሚሽኑን ተቋማዊ አቅም በመገንባት እና አስፈላጊውን የበጀት ግብዓት በማሟላት፣ በአገሪቱ አስተማማኝ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ሥርዓት እንዲሰፍን በጋራ ለመስራት ያለመ መሆኑን መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ያሳያል።



***የኢሰመኮ ዋና ኮሚሽነር ብርሃኑ አዴሎ፣ በአሥረጂ መድረኩ ላይ ማብራሪያዎችን በሰጡበት ወቅት፤***

ይኸው የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ በዚኹ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ግምገማውን ያደረገው **የአገራዊ ምክክር ኮሚሽንን** መሆኑን እንደራሴ ያሰባሰበችው መረጃ ይጠቁማል። የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ለ2019 በጀት ዓመት የ62.6 በመቶ የበጀት ጭማሪ ጥያቄ ያቀረበ ሲሆን፣ ኮሚሽኑ ከተቋቋመበት ትልቅ ዓላማ አንጻር በቀጣይ የፕሮግራም በጀትን ታሳቢ ያደረገ ዕቅድ ማቅረቡንም ቋሚ ኮሚቴው በጥንካሬ አንስቷል ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ፣ ተቋሙ በቀጣይ እያንዳንዱን ወጪ በቁጥር የተደገፈ እና ግልጽ በሆነ መልኩ እንዲያቀርብ አቅጣጫ ሲሰጡ፤ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም ዓለማየሁ በበኩላቸው፣ መንግስት የምክክር ሂደቱን ለማሳካት የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቅሰው፣ የበጀት ዕቅዱ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ መዘጋጀቱን አወድሰዋል።

የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነሩ አምባሳደር ማሃሙድ ድሪር በሰጡት ማብራሪያ፣ ባለፈው በጀት ዓመት በአንዳንድ አካባቢዎች የነበሩ የጸጥታ ኹኔታዎች ለመስክ ሥራዎች አለመመቸት የበጀት አጠቃቀም እና አፈጻጸም ዝቅተኛ እንዲሆን ምክንያት መሆኑን ከማንሳታቸው ባለፈ፣ ይኹን እንጂ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት እና ከሌሎች ዓለም ዓቀፍ አጋሮች የሚገኘው ድጋፍ ለታለመለት ዓላማ እየዋለ መሆኑን ጠቁመዋል ተብሏል።

ሰኔ ወር ላይ ለሚካሄደው እና 4 ሺሕ የሚጠጉ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚሳተፉበት አገራዊ ጉባኤ፣ ቀሪውን የ2018 በጀት በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል መታቀዱንም ሌሎቹ የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች ማስረዳታቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ጠቁሟል።



*የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም ዓለማየሁ፣ በአሥረጃ መድረኩ ወቅት፤*

ከላይ የተጠቀሱትን ሦሥቱን የፌደራል ተቋማት የ2018 በጀት አፈጻጸምን እና የ2019 በጀት ዓመት ፍላጎትን የገመገመው የፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የኢትዮጵያ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ያቀረበውን የ2018 በጀት ዓመት አፈጻጸም እና የ2019 በጀት ዓመት እቅድም መርምሯል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ፣ የግዴታ ወጪዎች ተብለው የሚመደቡት እንደ ደመወዝ፣ የቢሮ ኪራይ፣ የተሽከርካሪ ጥገና እና የነዳጅ ወጪዎች በግልጽ እና በዝርዝር ተለይተው መቅረብ እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም ዓለማየሁ በበኩላቸው፣ ተቋሙ የተጣለበትን ሕገ- መንግሥታዊ ተልዕኮ በብቃት መወጣት እንዲችል ተገቢው ሀብት ሊመደብለት እንደሚገባ ተናግረዋል ተብሏል። የተቋሙ ዋና ዕንባ ጠባቂ ወ/ሮ ስመኝ ውቤ በበኩላቸው፣ ተቋሙን ይበልጥ ለሕዝብ ተደራሽ ለማድረግ በደቡብ ክልል አንድ አዲስ ቅርንጫፍ፣ እንዲኹም በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች ኹለት ንዑስ ማዕከላትን ለመክፈት ማቀዳቸውን ጠቁመዋል። በተለይም አዲሱ የመረጃ ነጻነት ዐዋጅ ሲጸድቅ የሚመጡ ሰፊ ኃላፊነቶችን ለመወጣት፣ የመንግስት በጀት ድጋፍ ወሳኝ መሆኑንም ዋና ዕንባ ጠባቂዋ ጨምረው ተናግረዋል ተብሏል።



***የፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው፣ የኢትዮጵያ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የበጀት ጥያቄን ሲያደምጥ፤***

እኒኽን መሰል የፌደራል ተቋማቱን የበጀት አፈጻጸም እና የቀጣይ በጀት ዓመት የበጀት ዝግጅት ያደመጠው ምክር ቤቱ፣ **የጤና ሚኒስትር** ሚኒስትሯን ምላሽ እና ማብራሪያዎችም አድምጧል። ምክር ቤቱ በወሩ አጋማሽ ባካሄደው 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 20ኛ መደበኛ ስብሰባው፣ የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትሯ ዶክተር መቅደስ ዳባ፣ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸውን የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈፃፀም አስመልክቶ ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረቡት ጥያቄዎች የሰጧቸውን ምላሽ እና ማብራሪያ አድምጧል። የምክር ቤቱ አባላቱም፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ባለፉት ዘጠኝ ወራት በሽታዎችን ከመከላከል፣ መቆጣጠር እና ማከም አንፃር አበረታች ውጤት ማስመዝገቡን ገልጸው፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዘነጋ ያለ እና አምራች ዜጎችን የሚቀጥፍ የኤችአይቪ እና የቲቪ በሽታን የመከላከል እና መቆጣጠር ብቃት ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባም ጠቁመዋል።

ሚኒስትሯ ዶክተር መቅደስ ዳባም፣ የኤችአይቪ እና የቲቪ ወረርሽኞችን የመከላከል እና መቆጣጠር ሥራዎች በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ለረጅም ጊዜ በብዙ ፕሮግራሞች ሲደገፍ የነበረ ቢሆንም፣ አገልግሎቱ በተቋረጠ ጊዜ ኢትዮጵያ ጠንካራ የጤና ስርዓት በመገንባቷ ባለፉት ዓመታት በሽታዎችን በመከለል እና በመቆጣጠር ረገድ ውጤት መመዝገቡን አብራርተዋል ተብሏል። የግብዓት አቅርቦት እና ስርጭትን በተመለከተ በዲጂታል ሥርዓት ክትትል፣ ቁጥጥር እንዲኹም ተደራሽ የማድረግ ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚሰሩም ዶክተር መቅደስ ገልጸዋል። በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ከተቀመጡ ግቦች አንፃር አኹንም የሚቀሩ ሥራዎች አሉ ያሉት ሚኒስትሯ፣ የጤና ክብካቤ አሀድን ማጠናከር፣ የባለሙያዎችን ብቃት ማጎልበት፣ የመረጃ ስርዓቱን ማዘመን እና ተዓማኒ ማድረግ፣ የጤና ፋይናንስ ስርዓቱን ማጠናከር እንዲኹም በአገር ምርት እና በአገር ባለሙያ መጠቀም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸው በቀጣይ በትኩረት የሚሰራባቸው ዕቅዶች መሆናቸውን መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።



***የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትሯ ዶክተር መቅደስ ዳባ፣ የመሥሪያ ቤታቸውን ሪፖርት ሲያቀርቡ፤***

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በዚኹ ወርኃ ግንቦት፣ **የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን**ን

የ2018 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት እቅድ አፈፃፀምም ገምግሞ ነበር። የተቋሙን ሪፖርት ያደመጠው፣ በምክር ቤቱ የንግድ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን፤ ሰብሳቢዋ የተከበሩ ወ/ሮ አሻ ያሕያም፣ ከበጀት ዓመቱ ባሻገር የመካከለኛው ዘመን እቅድ የመጨረሻ ዓመት የተገኙ ውጤቶች ኮሚሽኑ ከቋሚ ኮሚቴው የሚሰጠውን ግብረ መልስ በእቅድ ይዞ እንደ ግብዓት መጠቀሙ አበረታች ለውጥ ለማምጣት እንዳስቻለው ገልፀዋል ተብሏል።

በሥራ እድል ፈጠራ፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር እና በውጭ ምንዛሪ ገቢ የተመዘገቡ ውጤቶች ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ አቅጣጫ መስጠታቸው የተጠቀሰው ሰብሳቢዋ፣ የአገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶችን በኹሉም የአገሪቱ አካባቢዎች እንዲንቀሳቀሱ እና ፕሮጀክቶች በፍጥነት ወደ ምርት እንዲገቡ የማድረጉ ሥራ ለአገር ገቢ እና ወጭ ምርት መጣጣም ያላቸው አስተዋፅዖም አበረታች መሆኑን ጠቅሰዋል ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዮሐንስ መስፍን በበኩላቸው፣ የአገልግሎት አሰጣጡን ፈጣን እና ቀልጣፋ ለማድረግ በመሶብ አንድ ማዕከል የኮሚሽኑን የተለያዩ አገልግሎቶች እንዲያገኙ መደረጉ አበረታች መሆኑን ከመጥቀሳቸው ባለፈ፣ በልዩ ኢኮኖሚ ዞኖች ያሉ ፋብሪካዎች በቴክኖሎጂ እና በፋይናንስ በመደገፍ ምርቶች በጥራት እና በብዛት እንዲመረቱ ቅንጅታዊ ሥራዎች የበለጠ ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባም ማሳሰባቸው ተሰምቷል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ዶ.ር. ዘለቀ ተመስገን በበኩላቸው፣ ኮሚሽኑ ለሥራ ማነቆ የሆኑ ዐዋጆችን በማሻሻል፣ አሰራርን የሚያሳልጡ አዳዲስ ዐዋጆችን በምክር ቤቱ በማፀደቅ ምቹ እና ተገማች የመዋዕለ-ንዋይ ከባቢን መፍጠር እንደተቻለ አብራርተዋል ተብሏል። በዘጠኝ ወራት ውስጥ የውጭ ቀጥተኛ መዋዕለ-ንዋይን በመሳብ 3.521 ቢሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን ያነሱት ኮሚሽነሩ፣ ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ብሎም በአፍሪካ ቀዳሚ የውጭ ቀጥተኛ የመዋዕለ-ንዋይ መዳረሻ ለመሆን በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን ለቋሚ ኮሚቴው አባላት ነግረዋቸዋል።



***የንግድ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዋ የተከበሩ አሻ ያሕያ፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ሪፖርት በቀረበበት ወቅት፤***

የወርኃ ግንቦት የመጨረሻ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት አቅራቢ የነበረው፣ **የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር** ሲሆን፤ የተቋሙን ሪፖርትም ያቀረቡትም ሚኒስትሩ ዶ.ር. በለጠ ሞላ ነበሩ። በምክር ቤቱ 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 22ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ የተገኙት ሚኒስትሩ፣ መሥሪያ ቤታቸው በዘጠኝ ወራት ውስጥ

ችግር ፈቺ ጥናት እና ምርምሮችን በማካሄድ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደቻለ ገልጸዋል።

ዘርፉ የኢትዮጵያን የ2030 የዘላቂ ልማት ግቦችን፣ እንዲኹም የ2063 አጀንዳን ለማሳካት ወሳኝ ድርሻ እንዳለው ተገንዝቦ በትኩረት ሲሰራ መቆየቱን ያነሱት ሚኒስትሩ፣ በዘጠኝ ወራት ውስጥ በኢኖቬሽን ዘርፉ 1714 የጥናት እና ምርምር ሥራዎች ተካሂደው የተሻለ ውጤት ተመዝግቧል ብለዋል ተብሏል። ሚኒስትሩ አክለውም፣ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ በኹሉም ስታርትአፖች 6,424 የሥራ እድሎች መፈጠራቸውንም ለምክር ቤቱ መናገራቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷቸዋል።

የጥናት እና ምርምር ዘርፎች ለአገሪቱ ዘርፈ-ብዙ ጥቅሞች እንዲያስገኙ ታቅዶ በትኩረት እየተሰራ እንደሆነም ያነሱት ዶ.ር. በለጠ፣ በዲጂታል 2030 በአገሪቱ ጠረፋማ አካባቢዎች የሳይል እና የኢንተርኔት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ተቋሙ ራዕይ አንግቦ እየሰራ እንደሆነም ገልጸዋል። በምክር ቤቱ የሰው ሀብት ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ በበኩላቸው፣ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የንግድ እና የመንግስት አገልገሎቶች በቴክኖሎጂ የተደገፉ እንዲሆኑ ያከናወናቸው ተግባራት አበረታች መሆናቸውን አስገንዝበዋል ተብሏል።



*የሰው ሀብት ስራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሪፖርት በተገመገመበት ወቅት*

የአገሪቱን ልማቶች ለማፋጠን የሚያግዝ ሳተላይት ለማምጠቅ እና የመንግስት አገልግሎቶችን ይበልጥ ለማሳለጥ የጥሪ ማዕከል ለመገንባት በእቅድ ተይዘው በዘጠኝ ወራት ውስጥ ያልተፈጸሙ ተግባራት መሆናቸውን ያነሱት ሰብሳቢው፣ መንግስት የጀመረውን የመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎት ለማሳደግ፣ የዲጂታል ኢትዮጵያ 2030 በሚገባ እንዲሳካ እንዲሁም በስፔስ ሳይንስ ዘርፍ ችግር ፈቺ ጥናቶች እንዲካሄዱ ተቋሙ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራ እንደሚገባም ማሳሰባቸው ተጠቅሷል።



*የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሚኒስትሩ ዶ.ር. በለጠ ሞላ፣ የተቋማቸውን ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት፤*

## 2.2 የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶች

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ በወርኃ ግንቦት ምንም እንኳን ምንም ዓይነት የመስክ ጉብኝት ባያደርጉም ቅሉ፣ የተወሰኑ ተቋማትን ይመለከታቸዋል ባሏቸው ቋሚ ኮሚቴዎቻቸው በኩል ጎብኝተዋል።

### የተቋማቱ ጉብኝቶች

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ግንቦት ወር፣ በሥድስት ተቋማት የመስክ ጉብኝቶችን ማድረጉን፣ ከምክር ቤቱ ያሰባሰበነው መረጃ ይጠቁማል።

በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ግንቦት ወር በምክር ቤቱ አባላት ከተጎበኙት ተቋማት መካከል በጊዜ ምጣኔ ቀዳሚው የሆነው፣ **የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻ እና ማከፋፈያ ድርጅት** ሲሆን፤ ተቋሙን የጎበኘውም በምክር ቤቱ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ነበር። የድርጅቱ ዋና ሥራ አሥፈፃሚ ዶ.ር. ተመስገን ጋሮማም፣ ተቋሙ የትምህርት ፖሊሲውን መሠረት በማድረግ ለትምህርት ዘርፉ በብቸኝነት ግብዓት በአገር ውስጥ በማምረት እና ከውጭ በመግዛት የሚያቀርብ ድርጅት መሆኑን ገልጸዋል።

የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መና በበኩላቸው፣ የትምህርት መሣሪያዎች ድርጅቱ ለኢትዮጵያ ትምህርት ዘርፍ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን በማምረት እና በማቅረብ በትምህርት ሥርዓቱ ላይ አስተዋጽዖ እያደረገ ያለ ተቋም መሆኑን ከመጥቀስ ባለፈ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ አገልግሎቱን በማዘመን እና የምርት ጥራቱን በማሻሻል በትምህርት ዘርፉ የማይተካ ሚና እየተጫወተ መሆኑን መናገራቸው ተጠቅሷል።

በተለይም ለመማር-ማስተማር ሂደት ወሳኝ የሆኑ መጻሕፍት፣ የሳይንስ መሳሪያዎች፣ የሕትመት ሥራዎች እና የትምህርት ቤት ቁሳቁሶችን በአገር ውስጥ በማምረት ለአገሪቱ የትምህርት ጥራት መሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑን የጠቆሙት ሰብሳቢው፣ ድርጅቱ ቀድሞ የነበሩበትን የፋይናንስ እና የአሥተዳደር ችግሮች በመሻገር ዛሬ ወደ ተሻለ የአፈጻጸም ደረጃ መድረሱ የሚበረታታ መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል።



*የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻ እና ማከፋፈያ ድርጅትን ሲጎበኙ፤*

በዚኹ ወርኀ ግንቦት፣ በምክር ቤቱ የከተማ፣ መሰረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ በተለያዩ የሕንጻ ግንባታ ፕሮጀክቶች የመስክ ምልከታ አካሄዷል። ቋሚ ኮሚቴው በመስክ ምልከታው **የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የፌዴራል ሰነዶች ማረጋገጫ ምዝገባ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን እና የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲን የሕንጻ ግንባታ ፕሮጀክቶች** ተዘዋውሮ መጎብኘቱን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቅሳል።

የፌዴራል ሕንጻዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ዳዊት መሓሪ፣ የሕንጻ ፕሮጀክቱ አፈጻጸም 70 በመቶ፣ እንዲኹም ፋይናንሺያል አፈጻጸሙ ደግሞ 58 በመቶ ላይ መድረሱን ለቋሚ ኮሚቴው አባላት አብራርተዋል። አኹን ላይ የፕሮጀክቱ አፈጻጸሙ 76 በመቶ ላይ መድረሱን የገለጹት ኢንጂነር ዳዊት፣ አጠቃላይ የግንባታ ፕሮጀክቱን እስከ መስከረም 30 ቀን 2019 ዓ.ም. ለማጠናቀቅ እቅድ ተይዞ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን አብራርተዋልም ተብሏል። በተመሳሳይም ቋሚ ኮሚቴው በፌዴራል ሰነዶች ማረጋገጫ ምዝገባ ኤጀንሲ የሕንጻ ፕሮጀክት የግንባታ ሂደትን የጎበኘ ሲሆን፣ የግንባታ አፈጻጸሙ 60 በመቶ፣ ፋይናንሺያሻል አፈጻጸሙ ደግሞ 53 በመቶ ላይ መድረሱን ተመልክቷል። ግንባታውም፣ እስከ ታኅሣሥ 30 ቀን 2019 ዓ.ም. እንደሚጠናቀቅ፣ የፕሮጀክቱ አማካሪዎች በዚያ ላገኟቸው የኮሚቴው አባላት ጠቅሰውላቸዋል።

የወሩን ጉብኝቱን በእነዚኽ ተቋማት ብቻ ያላበቃው ቋሚ ኮሚቴው፣ በኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የሕንጻ ግንባታ ፕሮጀክትን ጎብኝቷል ተብሏል። በዚኽ ጉብኝቱም፣ የፕሮጀክቱ አጠቃላይ አፈጻጸም 80 በመቶ ላይ መገኘቱን መረዳቱ ባለፈ፣ ግንባታውም በ2019 በጀት ዓመት መጀመሪያ ወራት ውስጥ ተጠናቆ ለአገልግሎት እንደሚበቃም ተገልጾለታል ተብሏል። ወደ ኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲም ጎራ ያለው ቋሚ ኮሚቴው፣ የዩኒቨርሲቲው የሕንጻ ግንባታ አፈጻጸሙ 87 በመቶ፣ ፋይናንሺያል አፈጻጸሙ ደግሞ 65 በመቶ ላይ መድረሱን ማረጋገጥ ችሏል ተብሏል።

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ.C. ተሾመ ነቃጥበብም፣ የዩኒቨርሲቲው አዳዲስ የሕንጻ ፕሮጀክት ግንባታዎች በተሻለ ፍጥነት እየተጠናቀቁ መሆናቸውን ገልጸው፣ ያረጁ ሕንጻዎች አደጋ ከማድረሳቸው በፊት ለታሪክ የሚቀመጡ እና የሚፈርሱትንም በጥናት ለመለየት በጀት የሚያሰፈልግ መሆኑን ለቋሚ ኮሚቴው አባላት

መናገራቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ጠቅሷቸዋል።



*የከተማ፣ መሰረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የሕንጻ ፕሮጀክቶቹን በጎበኙበት ወቅት፤*

## 3. የፓርላማው ዲፕሎማሲ

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ በወርኃ ግንቦት ከከወኗቸው ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነቶች መካከል አንዱ፣ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲን የተመለከተው ነበር። በዚኽም፣ በዚኹ ወር ሦሥት ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲዎችን ከውነዋል።

የሕዝብ ተወካዮቹ የወሩ ቀዳሚ የፓርላማ ዲፕሎማሲ ክንውን የነበረው፣ በምክር ቤት **የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች እና የሰው ኃብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ በቻይና ብሔራዊ ሕዝባዊ ኮንግረስ የትምህርት፣ ሳይንስ፣ የባህል እና የኅብረተሰብ ጤና ኮሚቴ ሊቀመንበር ሚስተር ሉኦ ሹጋንግ የተመራ የልዑክ ቡድን ጋር** መወያየታቸው ነበር።

የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎም፣ ኢትዮጵያ እና ቻይና ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ ታሪካዊው ግንኙነት እንዳላቸው አውስተው፣ ይኽንን ግንኙነት አጠናክሮ መቀጠል ይገባልም ብለዋል ተብሏል። ኢትዮጵያ በአኹኑ ወቅት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ካላቸው አገራት መካከል አንዷ መሆኗን ያነሱት ሰብሳቢው፣ ቻይና የኢትዮጵያን ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ለማፋጠን ከፍተኛ ሚና የምትጫወት አገር መሆኗን አስገንዝበዋል።

በአኹኑ ወቅት የቻይና ቀጥተኛ የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት እና የኹለቱ አገራት የንግድ ግንኙነት 5 ቢሊዮን ዶላር መድረሱን ያነሱት የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ፣ ከ2 ሺሕ በላይ የቻይና ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ተደርገው ከ560 ሺሕ በላይ ለሚሆኑ ኢትዮጵያውያን የሥራ እድል መፍጠር መቻላቸው የአገራቱን ጠንካራ ስትራቴጂካዊ ግንኙነት ማሳያ መሆኑንም በውይይቱ ወቅት መናገራቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ጠቅሷቸዋል።

በዚያው ውይይት የተገኙት የሰው ኃብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ በበኩላቸው፣ ቻይና ለበርካታ ኢትዮጵያውያን የሥራ እድል በመፍጠር እና የእውቀት ሽግግር በማድረግ በሰው ኃብት ልማት ዘርፍ ለአገሪቱ ዕድገት የበኩሏን ሚና እየተወጣች ትገኛለች ብለዋል። ቻይና ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ50 በላይ ለሚሆኑ አገራት ከቀረጥ ነጻ የገበያ እድል መስጠቷን አክለው ያነሱት የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ፣ ይኽንን እድል በመጠቀም የኢትዮጵያን ምርቶች በብዛት ወደ ቻይና በመላክ አገሪቱ ተጠቃሚ እንድትሆን መስራት ይገባልም ብለዋል ተብሏል።



*የኹለቱ ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ ከቻይናው ልዑክ ጋር፤*

የወሩ የምክር ቤቱ አባላት ሌላይኛው ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ የነበረው፣ **“ከዲጂታል መሠረተ-ልማት ወደ ዲጂታል የሕዝብ ሥነ-ምኅዳር”** በሚል ርዕስ፣ በኮትዲቯር በተካሄደው አህጉራዊ ጉባኤ ላይ መገኘታቸው ነበር። የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ለዜጎች አገልግሎት አሰጣጥ፣ ለታማኝ የዳታ ልውውጥ እና ለአህጉራዊ የኢኮኖሚ ትስስር ያለውን አይነተኛ ፋይዳ የሚመለከቱ አጀንዳዎች ላይ ሰፊ ምክክር ተደርጎበታል በተባለው በዚኹ ጉባኤ ላይ የተገኙት፣ በምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማሕዲ በሰጡት አስተያየት፣ ኢትዮጵያ የጀመረችው የፋይዳ ብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ፕሮግራም፣ ለአገራዊ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን እና ለዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ መሰረት እየጣለ መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል።

ምክትል ሰብሳቢው አክለውም፣ የዘንድሮው ጉባኤ ትኩረት ያደረገባቸው የዲጂታል ሥነ-ምኅዳር ግንባታ እሴቶች ከኢትዮጵያ የዲጂታል ስትራቴጂ ጋር በእጅጉ የሚጣጣሙ መሆናቸውን አንስተው፣ በተለይም የሕግ ማዕቀፎችን ማጠናከር፣ የዳታ ግላዊነትን ማረጋገጥ እና ድንበር ተሻጋሪ የዲጂታል መታወቂያ ትስስርን መፍጠር ለቀጠናዊ ሰላም እና ለኢኮኖሚ ውህደት ያለውን አስፈላጊነት ለጉባኤው እድምተኞች ማስገንዘባቸውን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ጠቅሷቸዋል። በዋና ከተማዋ አቢጃን በተካሄደው በዚኹ ጉባኤም፣ ከተለያዩ የአፍሪካ አገራት የተውጣጡ ከ2 ሺሕ በላይ ተሳታፊዎች፣ ፖሊሲ አውጪዎች እና የቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ተሳታፊ ነበሩም ተብሏል።




*የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማሕዲ እና የጉባኤው እድምተኞች በከፊል፤*

የወሩ የመጨረሻው የሕዝብ ተወካዮቹ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ የነበረው፣ ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ወደብ ለማግኘት የምታደርገውን ጥረት አገረ-ፊንላንድ እንደምትደግፍ የተነገረበት ኹነት ነበር። ኹነቱም፣ በምክር ቤቱ **የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ከፊንላንድ ፓርላማ አባሉ ኪምሞ ኪልጂ እና በኢትዮጵያ ከፊንላንድ አምባሳደሩ ሲኒካ አንቲላ ጋር የተወያዩበት** ነበር።

የቋሚ ኮሚቴው አባል የተከበሩ አምባሳደር ዲና ሙፍቲም፣ አገራቱ ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ ታሪካዊ

ግንኙነት እንዳላቸው አስታውሰው፣ ይኽንን ግንኙነት በይበልጥ ማጠናከር እንደሚገባ አስገንዝበዋል ተብሏል። ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ሰላምን ለማስፈን እና ቀጠናዊ ልማት እና ኹለንተናዊ ብልፅግናን ለማረጋገጥ ከኢጋድ ጋር በጋራ እያደረገች ያለችውን ጥረት ለሉዑኩ ያስረዱት አምባሳደሩ፣ ኢትዮጵያ ከታሪክ፣ ከመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ከሕዝብ ብዛት እና ምጣኔ ሀብታዊ እድገት አንጻር እየጎላ የመጣውን የባሕር በር ፍላጎቷን በማንሳት የኢትዮጵያን አቋም ለፊንላዱ ልዑክ አስረድተዋል። ኢትዮጵያ የባሕር በር ለማግኘት የምትከተለው ስልት ሰላማዊ፣ በሰጥቶ መቀበል መርህ ላይ የተመሠረተ፣ የአካባቢውን አገራት ተጠቃሚ ሊያደርግ በሚችል መልኩ፣ በዲፕሎማሲያዊ እና በስምምነት መሆኑንም ማስረዳታቸው ተጠቅሷል። የፊንላንድ ፓርላማ አባል ኪምሞ ኪልጁን በበኩላቸው፣ በፊንላንድ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ውስጥ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀዳሚዋ እና ቁልፍ አገር መሆኗን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ብሎም በአፍሪካ ሽብርተኝነትን ለመከላከል እና ሰላም እና ደኅንነትን ለማምጣት ለምታደርገው ጥረት አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር ለመተባበር ያላትን ዝግጁነት የጠቀሱት እንደራሴው፣ ኢትዮጵያ በሰላማዊ እና ዲፕሎማሲያዊ በሆነ መንገድ ወደብ ለማግኘት የምታደርገውን ጥረት አገራቸው እንደምትደግፍም መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል። በኢትዮጵያ የፊንላንድ አምባሳደር ሲኒካ አንቲላ በበኩላቸው፣ አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር በዲጅታላይዜሽን ዘርፍ፣ በቴሌ-ኮሙዩኒኬሽን እና በሶላር ኢነርጅ በትብብር እየሰራች መሆኑን ጠቁመው፣ በቀጣይም ይኽንኑ አጠንክራ እንደምትቀጥል ተናግረዋል ተብሏል።



*የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላቱ፣ ከፊንላንድ ፓርላማ አባሉ እና ከአምባሳደሩ ጋር በተወያዩበት ወቅት፤*

## 4. እንደራሴዎቹ ስለ‘ራሳቸው በ‘ራሳቸው

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ በዚኹ ግንቦት ወር ያከናወኗቸው ተግባራት ከላይ ያነሳናቸውን ሕገ-መንግሥታዊ ኀላፊነቶቻቸውን ብቻም ሳይሆን፣ ምክር ቤታቸውን የተመለከቱ በጀት ተኮር ተግባራትን እንደነበርም በወሩ የተሰባሰቡት የምክር ቤቱ መረጃዎች ያሳያሉ።

በጊዜ ምጣኔ፣ የምክር ቤቱ አባላት በቀዳሚነት የገመገሙት፣ የምክር ቤቱን የ9 ወራት የሥራ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ነበር። እንደሚታወቀው ባሳለፍነው ሚያዚያ ምክር ቤቱ፣ የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት የዘጠኛ ወራት እቅድ አፈጻጸም የገመገመ ሲሆን፤ ይኸኛውን የምክር ቤቱን ሪፖርትም ያቀረቡት፣ በምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የዋና ጸሐፊው ተወካይ እና የአሥተዳደር ዘርፍ ምክትል ዋና ጸሐፊው ክረዩ ባናታ ሲሆኑ፤ ሪፖርቱን ያደመጡት አፈ ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ በምክር ቤቱ የተመሩ ረቂቅ ዐዋጆች የምርመራ ሂደታቸው ተጠናቆ ሪፖርት እና የውሳኔ ሐሳብ ለምክር ቤቱ መቅረብ እንዳለበት አሳስበዋል ተብሏል።

ቋሚ ኮሚቴዎች ችግሮችን በተናጠል ከመፍታት ይልቅ በቅንጅት እና በትብብር መስራት እንዳለባቸውም ጨምረው የጠቀሱት አፈ-ጉባኤው፣ የፓርላማ የጥናት እና የምርምር ውጤቶች በተግባር ላይ መዋላቸውን አስመልክቶ በቀጣይ በልዩ ትኩረት እንደሚገመገም አመላክተዋል። የምክር ቤቱ የአማካሪ እና የአሥተባባሪ ኮሚቴ አባላት በበኩላቸው፣ በሕግ አወጣጥ ሂደት ባለፉት 9 ወራት 13 የሚደርሱ ሕግጋት መጽደቃቸውን ገልጸው፣ በተለይም ለበርካታ ዓመታት ሰፊ ምርመራ ሲደረግበት የነበረው የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ ጸድቆ ወደ ተግባር መግባቱን ጠቁመዋል ተብሏል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት እና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤቶችን የ2019 በጀት ዓመት ዕቅድ እና የበጀት ጥያቄ መመርመሩም፣ የእንደራሴዎቹ አንዱ የወሩ የ‘ራስ በ‘ራስ ክንውን ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ፣ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በትብብር በመስራት ወጪዎች የሚቀነሱበት ኹኔታዎች ካሉ ማየት የሚቻልበት ኹኔታ እንዲኖር አቅጣጫ ከማስቀመጣቸው ባለፈ፣ አይቀሬ ተብለው የሚታወቁ ወጪዎችን መለየት ቢቻል ለሥራ አመቺ እንደሚሆን ጠቅሰዋል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም አለማየሁ፣ ለበጀቱ የእቅድ ዝግጅት እንዲረዳ የበጀት ጭማሪውን ያስከተሉ ምክንያቶች በግልፅ ሁኔታ መለየት እንደሚያስፈልግ አንስተው፣ በጀት ሲሰራም ከጣራው ጋር ማነፃፀር ጠቃሚ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት የጽሕፈት ቤቱ ምክትል ኃላፊ ዶ.ር. በላይ ወዳሾ በበኩላቸው፣ የበጀት ጭማሪው

በዋናነት በሦሥት ዘርፎች ተከፍሎ መታቀዱን ጠቅሰው፤ እንደ ነዳጅ ያሉ በዓለም ዓቀፍ ገበያ የዋጋ ንረት የታየባቸው ግብዓቶች፣ አዳዲስ የሰው ኃይል ቅጥሮች እንዲኹም የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓል አከባበር ወጪዎች የበጀት ጭማሪው ምክንያቶች መሆናቸውን በውይይቱ ላይ መናገራቸው ተሰምቷል።

ሪፖርት አቅራቢው ከረዩ ባናታ በበኩላቸው፣ ለቴሌቪዥን ሥርጭት፣ ለቤተ-መጸሕፍት ማስፋፊያ እና ለዲጂታላይዜሽን ሥራዎች የሚወጡ ወጪዎች ከታሰበው በላይ በመጨመራቸው የበጀት ጭማሪ ማስፈለጉን ገልጸዋል። ከዚኽ በተጨማሪም፣ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎች ግዥ፣ የሲስተም ዝርጋታ እና የፕሮቶኮል አልባሳት የዋጋ ንረት በበጀት ዝግጅቱ ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩን ከረዩ አብራርተዋል ተብሏል።



*በምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የዋና ጸሐፊው ተወካይ እና የአሥተዳደር ዘርፍ ምክትል ዋና ጸሐፊው ከረዩ ባናታ፣ ሪፖርቱን ሲያቀርቡ፤*

**በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተመራጭ ሴቶች ኮከስ** ሥራ አሥፈጻሚ፣ የኮከሱን የ2018 በጀት አመት የ10 ወራት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት መገምገሙም፣ እንዲሁ የእንደራሴዎቹ የወሩ የ'ራስ በ'ራስ ክዋኔ ነበር። በግምገማው ወቅትም፣ የምክር ቤቱ ምክትል አፈ-ጉባኤ እና የኮከሱ የበላይ ጠባቂ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ፣ ለኮከስ አባላቱ የተሰጡ የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች በምክር ቤቱ ሕግ አወጣጥ፣ በክትትል እና ቁጥጥር፣ በውክልና ሥራ እንዲኹም በፓርላማ ዲፕሎማሲ ሥራዎች ረገድ ተጨባጭ ውጤት ያስገኙ በመሆኑ ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል ብለዋል ተብሏል።

ከ2019 እስከ 2023 ዓ.ም. ያለውን የኮከሱን የስትራቴጅ ዕቅድ እና የ2019 ዓ.ም. መነሻ ዕቅድ በማዘጋጀት ለቀጣዩ ምክር ቤት መሰረት መጣል ይገባል ሲሉም አሳስበዋል። ሪፖርቱን ያቀረቡት የኮከሱ ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ አለሚቱ አበበ በበኩላቸው፣ በተለያዩ ጊዜያት በተከናወኑ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች የተሻለ ግንዛቤ በመፈጠሩ የሴት እንደራሴዎቹን የመፈጸም እና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ ተችሏል ማለታቸው ተጠቅሷል።



*የምክር ቤቱ ምክትል አፈ-ጉባኤ እና የኮከሱ የበላይ ጠባቂ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ፣ በውይይቱ ወቅት፤*

## 5. ኢትዮጵያ ምን ተስማማች?

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ በዚኹ ግንቦት ወር ኹለት የብድር ስምምነቶችም ይጸድቁ ዘንድ ፈቃዳቸው ሆኗል። በዚኽ ወር ምክር ቤቱ ባካሄደው 23ኛው መደበኛ ስብሰባው ያጸደቃቸው ስምምነቶች፣ **በኢትዮጵያ እና በአፍሪካ ልማት ባንክ እና በኢትዮጵያ እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረጉት የብድር ስምምነቶች** መሆናቸው ተመልክቷል። የብድር ስምምነቶቹን በማስመልከት ማብራሪያዎችን የሰጡት፣ በምክር ቤቱ የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚኒስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ፣ ከአፍሪካ ልማት ባንክ ለአርብቶ አደር ምግብ እና የኑሮ ዘይቤ ማሻሻያ ፕሮጀክት የተገኘው ብድር፣ መንግስት የአርብቶ አደሩን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ለመቋቋም የሚያስችሉ የተቀናጁ የልማት ፕሮጀክቶችን የበለጠ እንደሚያግዝ ተናግረዋል ተብሏል።

ሚኒስትሩ አክለውም፣ ይኽንን የልማት ተግባር ይበልጥ ለማጠናከር እና ተጨማሪ የልማት ሥራዎችን በማካተት የአርብቶ አደሩን የአደጋ ተጋላጭነትን የመቋቋም አቅም ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ፣ ከአፍሪካ ልማት ባንክ የ71 ሚሊዮን 940 ሺ ዶላር ድጋፍ መገኘቱን ተናግረዋል። በብድር የተገኘው ገንዘብ የውኃ መሠረተ ልማቶችን፣ የእንስሳት ጤና አገልግሎቶችን፣ ዘላቂ የመሬት አያያዝን፣ ታዳሽ የኃይል አማራጮችን እና የአየር ትንበያ ጣቢዎችን ለማስፋፋት እንደሚውል የጠቀሱት ሚኒስትሩ፤ ብድሩ ከወለድ ነጻ እና የዐሥር ዓመት የችሮታ ጊዜን ጨምሮ በ40 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ የሚጠናቀቅ መሆኑን መናገራቸው ተጠቅሷል። ምክር ቤቱም፣ የብድር ስምምነቱን ዐዋጅ ቁጥር 1423/2018 ሲል በሙሉ ድምጽ አጽድቆታል።



*በምክር ቤቱ የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚኒስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ፣ የብድር ስምምነቶቹን ሲያብራሩ፤*

በተያያዘም፣ እኚኹ የመንግስት ዋና ተጠሪው የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በኢትዮጵያ እና በዓለም ዓቀፍ ልማት ማኅበር መካከል፣ ሥድስተኛውን ምዕራፍ ልማታዊ የሴፍትኔት ፕሮጀክት በማስመልከት እንደገለጹት፣ መንግስት በምግብ ዕጥረት ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ከዕርዳታ ተጠቃሚነት ወደ ምርታማነት ለማሸጋገር ባለፉት ጊዜያት የልማት ሴፍትኔት ፕሮጀክትን ቀርጾ ተግባራዊ ማድረጉን እና ሥድስተኛው ምዕራፍ ልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮጀክት በ12 ክልሎች እና በአንድ ከተማ አሥተዳደር ውስጥ ባሉ 494 ወረዳዎች ተግባራዊ ይሆናል ብለዋል ተብሏል።

ምክር ቤቱም፣ በኢትዮጵያ እና በዓለም ዓቀፉ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት፣ ዐዋጅ ቁጥር 1424 /2018 አድርጎ በአንድ ድምጸ ተዓቅቦ፣ በአብላጫ ድምጽ አጽድቆታል፡፡

## 6. የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታ፦ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የንግድ ፖሊሲ ዙሪያ

ኢትዮጵያ የንግድ ሥርዓቷን ያዘምናል፣ ተወዳዳሪነቷን ያጠናክራል እንዲኹም የረጅም ጊዜ የወጪ ንግድ ዕድገቷን ይደግፋል የተባለለትን የመጀመሪያውን ወጥ ብሔራዊ የንግድ ፖሊሲ፣ ግንቦት 18 2018 ዓ.ም. በሚኒስትሮች ምክር ቤት አማካኝነት አፅድቃለች። ይኽ ኹነት፣ አገሪቱ የንግድ ሚኒስቴርን ካቋቋመችበት የ118 ዓመታት ረጅም ታሪኳ ውስጥ፣ ራሱን የቻለ እና ወደ ነፃ ገበያ ሥርዓት ይመራል የተባለለት ወጥ የፖሊሲ ሰነድ ያገኘችበት የመጀመሪያው ታሪካዊ አጋጣሚ ሆኖ ተመዝግቧል። ከዚኽ እና ሌሎች ለዐብይ ኢኮኖሚው ተያያዥ ፋይዳ ያላቸውን ርዕሰ-ጉዳዮች አስመልክቶ፣ ብሪጅ ይኽንኑ ፖሊሲ ሳምንታዊ ዳሰሳዋ ልታደርገው መርጣለች፤ ከዚኽ ባለፈም፣ ፖሊሲው እንዳስቀመጠው፣ ማሻሻያ ያስፈልጋቸዋል የተባሉ ዐዋጆች እንደመኖራቸው፣ ይኽም በቀጥታ የሚመለከተው የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን ነውና፣ ይኽ የዳሰሳው መፍዔ ከመሆኑ ባለፈ፣ ዳሰሳዊ ምልከታችንም ይኽንኑ ነጥብም ያካትት ዘንድ ግድ ሆኗል።

ቀደም ሲል ወጥ የሆነ የንግድ ፖሊሲ አለመኖሩ እና የንግድ ሕግጋቱ በተለያዩ ዐዋጆች እና መመሪያዎች ውስጥ ተበታትነው መገኘታቸው፣ በገቢ እና ወጪ ንግድ መካከል ቅንጅት እንዳይኖር ከማድረጉም በላይ፣ በንግድ ሥርዓቱ ላይ ፍትሓዊ ውድድር እንዲጠፋ፣ ሕገ-ወጥነት እንዲስፋፋ እና ሸማቾች ለከፍተኛ ምሬት እንዲዳረጉም በምክንያትነት ሲጠቀስ ሰንብቷል።

### 6.1 ስለ ፖሊሲው ከተነገሩት

በአኹኑ ወቅት የጸደቀው ፖሊሲ፣ ከላይ እንደመነሾ የተጠቀሱትን መዋቅራዊ ክፍተቶች በመሙላት፣ የአገር ውስጥ እና የውጭ ንግድ አሠተዳደርን በቅጡ ለመምራት፣ የወጪ ንግድን በማዘመን ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ፣ የአገር ውስጥ አምራቾችን በታሪፍ እና በማበረታቻዎች ለመደገፍ እንዲኹም የሸማቾችን መብት እና ደኅንነት ለመጠበቅ አጅጉን አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷልም ተብሏል። ይኽ አዲስ ብሔራዊ የንግድ ፖሊሲ በዋናነት በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ፣ በትብብር እና ቅንጅት፣ በግልፅነት እና ተገማችነት እንዲኹም በፍትሓዊ ውድድር መርሆዎች ላይ ስለመሆኑም፣ ራሱ ሰነዱ ይጠቅሳል።

የሰነዱ አጠቃላይ ይዘትም የሀገር ውስጥ የግብይት ሥርዓትን ማዘመን፣ የገቢ እና ወጪ ንግድ አስተዳደር ማዕቀፍን ማጠናከር፣ ፍትሓዊ ንግድን ማስፈን እና የዲጂታል ንግድ ሥርዓት መገንባት ላይ ያተኩራል። ፖሊሲው በንግዱ ማኅበረሰብ ላይ ከፍተኛ መተማመንን በመፍጠር፣ የውጭ መዋዕለ-ንዋይን በመሳብ እና የአገሪቱን የንግድ ምኅዳር ወደ አዲስ ምዕራፍ ያሸጋግራል ተብሎም ተስፋ ተጥሎበታል።

ከዚኽም በተጨማሪ የወጪ ንግዱ በተበታተነ ኹኔታ በበርካታ ተቋማት የሚመራ በመሆኑ፣ በዓለም ዓቀፍ ገበያ ተወዳዳሪነቱን ማረጋገጥ ሳይችል መቆየቱም በብዙ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ዘንድ ሲነሳ ቆይቷል። ፖሊሲው የሀገር በቀል ዐብይ ኢኮኖሚ ማሻሻያ እና የዐሥር ዓመቱን የልማት ዕቅድ መነሻ አድርጎ የተዘጋጀ በመሆኑ አገራዊ ፋይዳው እጅግ የጎላ ነውም ተብሏል። ይኽ ሰነድ በአኹኑ ወቅት መዘጋጀቱ እና መጽደቁ በንግዱ ማኅበረሰብ እና በግሉ ዘርፍ ላይ ከፍተኛ ተገማችነትን እና መተማመንን መፍጠሩ አሌ ባይባልም፣ የግሉ ዘርፍ የአገሪቱ ዐብይ ኢኮኖሚ ዋንኛ አንቀሳቃሽ ሆኖ እንዲያገለግል መንግስት ምቹ ከባቢያዊ ኹኔታን እንደሚፈጥርም ይታመናል። በተለይም የንግድ ሕግጋት፣ ደንቦች እና አሠራሮች በየጊዜው ከመለዋወጥ ወጥተው፣ ለኹሉም የንግድ ተዋናዮች ግልጽ፣ ተጠያቂነት የሰፈነባቸው እና ቀድሞ ተገማች እንዲሆኑ ያደርጋል እንደመባሉ፣ የግሉ ዘርፍ ተለዋዋጭ በሆነው ዓለም ዓቀፍ የንግድ ምኅዳር ውስጥ የረጅም ጊዜ ዕቅዶቹን በተረጋጋ ኹኔታ እንዲመራ እና የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰቱን እንዲያስፋፋ ሙሉ መተማመንን ይፈጥርለታል የሚል መታመን እንዲኖርም አድርጓል።

ከዚኽ ባለፈም፣ ኢትዮጵያ በአኹኑ ወቅት የምታካሂደውን የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት ድርድር፣ የአህጉራዊ እና የቀጣናዊ የንግድ ስምምነቶች ውህደትን ወጥ በሆነ ማዕቀፍ ለመምራት የሚያስችል ሰነድ ከመሆኑ አኳያም፣ የውጭ ቀጥታ መዋዕለ-ንዋይን በመሳብ ረገድ ለድንበር ተሻጋሪ የንግድ ተቋማት እና ባለሀብቶች ከፍተኛ ተገማችነትን የሚሰጥ መሆኑም በበጎነት ተነስቷል።

ግንቦት 18 የጸደቀው ይኽ ፖሊሲ የመጣው፣ የኢትዮጵያ የንግድ ዘርፍ ለብዙ ዐሥርታት በአንድ ወጥ ብሔራዊ ማዕቀፍ ከመመራት ይልቅ፣ በተበታተኑ ሕግጋት፣ መመሪያዎች እና አሥተዳደራዊ አሠራሮች ስር ሲሠራ ከቆየ በኋላ ነው። አጠቃላይ የንግድ ፖሊሲ አለመኖሩ ለአሠራር መጓተት፣ ለሕግጋት አለመጣጣም እና አገሪቱ በግል እና በዓለም ዓቀፍ ገበያ ላይ በብቃት እንዳትወዳደር ማነቆ ሆኖ መቆየቱንም፣ ርዕሰ-ጉዳዩ በቀጥታ ይመለከታቸዋል የተባሉት ባለሥልጣናት ሲናገሩ ተደምጠዋል።

የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትሩ ዶ.ር. ካሳሁን ጎፌም በሰነዱ ዙሪያ ሲናገሩ፣ አዲሱ ፖሊሲ በኢትዮጵያ የንግድ ሥርዓት ውስጥ የላቀ መረጋጋት እና ወጥነትን ለማምጣት የታቀደ ነው ብለዋል። እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፣ ማዕቀፉ በተደጋጋሚ የሚደረጉ የሕግ ለውጦችን በመቀነስ ለነጋዴው ማኅበረሰብ ግልጽ እና አስቀድሞ ሊገመት የሚችል የሥራ አካባቢን ይፈጥራል ከማለታቸው ባለፈ፣ መንግስት ይኽንን ፖሊሲ የኢትዮጵያን የወጪ ንግድ መዋቅር ለመቀየር እንደ ትልቅ እርምጃ እንደሚያየውም አንስተዋል።

ለዐሥርታት የአገሪቱ የወጪ ንግድ በዋናነት ባልተቀነባበሩ የግብርና ምርቶች ላይ የተመሰረተ ከመሆኑ አኳያም፣ በአዲሱ ስትራቴጂ ስር ግን የውጭ ምንዛሬ ገቢን ለማስፋፋት ሲባል ማኑፋክቸሪንግን፣

እሴት የተጨመረባቸው ምርቶችን፣ የአገልግሎት ዘርፍ የውጭ ንግድን እና ቱሪዝምን ማሳደግም ዋንኛ ዓላማ መደረጋቸውን ሚኒስትሩ ሲናገሩ ተደምጠዋል። ይኽ ዓይነቱ የንግድ ብዝሓነት የኢኮኖሚውን የመቋቋም አቅም ለማጠናከር እና በዓለም ዓቀፍ የሸቀጦች ገበያ መዋዠቅ ላይ ያለውን ተጋላጭነት ለመቀነስ አስፈላጊ መሆኑንም ባለሥልጣናቱ ይከራከራሉ።

ፖሊሲው የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች በዕድገት ምዕራፋቸው ላይ ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ ጊዜያዊ የቀረጥ ጥበቃዎችን እና የታለሙ የማበረታቻ ሥርዓቶችንም ያስተዋውቃል ተብሏል። ይኽም ገና ወደ ገበያው ብቅ ያሉ ኢንዱስትሪዎች ወደ ሙሉ ዓለም ዓቀፍ ውድድር ከመግባታቸው በፊት ምርታማነታቸውን እና ተወዳዳሪነታቸውን እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል ተብሏል።

የብሔራዊ የንግድ ፖሊሲው መጽደቅ ትልቅ ምዕራፍ ቢሆንም፣ አኹን ትኩረቱ ወደ ትግበራ ዞሯል። የማሻሻያው ውጤታማነት በመጨረሻ የሚለካው ተወዳዳሪነትን በማሻሻል፣ ላኪዎችን በመደገፍ፣ መዋዕለ-ንዋይን በመሳብ እና የኢትዮጵያን ተሳትፎ በምሥራቅ አፍሪካ እና በዓለም ዓቀፍ ገበያ ላይ በማስፋፋት ባለው አቅም መሆኑ ግን የሚያጠራጥር ጉዳይ አይደለም።

## 6.2 ፖሊሲው ምን ይዟል?

በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ የሚመራው የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ ላለፉት ዐሥርታት የነበረውን የሕግ እና የቁጥጥር ክፍተት ለመሙላት ለሣሥት ዓመታት የተደረገውን ውይይት በማጠናቀቅ፣ የኢትዮጵያን የመጀመሪያውን ወጥ የንግድ ፖሊሲ አጽድቋል። ይኽ ባለ 48 ገጽ ሰነድ፣ የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሸማቾች ጥበቃ ማዕቀፎችን ሙሉ በሙሉ እንዲያሻሽል ሥልጣን የሚሰጥ ሲሆን፣ በተለይም የገበያ መዛባትን እና ጥራታቸውን ያልጠበቁ ምርቶች መስፋፋትን ለማስወገድ የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ ዐዋጅም በጥብቅ እንዲሻሻል ያዝዛል።

ፖሊሲው የቁጥጥር ሥርዓት ውስብስብነትን ዋነኛ ማነቆ አድርጎ የለየ ሲሆን፣ የምዝገባ እና የፈቃድ አሰጣጥ ሂደቶችን በዲጂታል ሥርዓት በማስደገፍ የንግድ ወጪዎችን ለመቀነስም ያልማል። በአምራች እና በሸማች ዋጋ መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት ለመፍታትም፣ ቀጥተኛ ትስስርን የሚያመቻቹ በተለምዶ "የእሁድ ገበያዎችን" የተሰኙትን ማስፋፋት እና ዘመናዊ የገበያ መሠረተ ልማቶችን መገንባት እንደ ስትራቴጂያዊ ጣልቃ ገብነት አካትቷል። እነዚኽ ማሻሻያዎች ከፍተኛ የዋጋ ንረትን በመቆጣጠር እና በሕጋዊው እና በትይዩ ገበያው የውጭ ምንዛሬ ተመኖች መካከል ያለውን ልዩነት በማጥበብ፣ የሕዝቡን የመግዛት አቅም ለመጠበቅ ከተቀመጠው የዐብይ

ኢኮኖሚ ዕቅዶች ጋር የተሳሰሩ መሆናቸውንም ሰነዱ ይጠቅሳል።

ይኸ የንግድ ፖሊሲ ሰነድ፣ በደንቦች እና መመሪያዎች አፈጻጸም ላይ የሚስተዋሉ የአሰራር ወጥነት ችግሮችን ለመቅረፍ፣ ያልተጠበቁ ተደጋጋሚ የደንብ ለውጦችን፣ ሕገ-ወጥ የንግድ ተግባራትን እና ዋጋ አሳንሶ የመላክ ወይም አስበልጦ የማስመጣት ችግሮችን ለመፍታትም ያለመ ነው። ከዚኽ ባለፈም፣ በትራንስፖርት እና የሎጂስቲክስ አቅርቦት ላይ ያሉ እጥረቶችን፣ የድንበር ላይ መዘግየቶችን እና ተደጋጋሚ የወረቀት ስራዎችን በበርካታ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ቅንጅት ለማስወገድ እንዲኹም የአገሪቱን ምርታማነት እና የማምረት ብቃት በማሳደግ የወጪ ምርቶችን በዓይነት እና በመጠን በማስፋት የውጭ ገቢን ለመጨመር እና የውጭ ቀጥታ መዋዕለ-ንዋይ መሳብ ላይ ትልቅ ትኩረት ማደርጉን ከሰነዱ መረዳት ይቻላል።

የገበያ ተደራሽነትን ማስፋት እና የወጪ ንግድን ማብዛት ስትራቴጂዎችን በተመለከተ የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት ድርድርን ማጠናቀቅ እና የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነትን ተግባራዊ ማድረግን፣ ኢ-መደበኛ የድንበር ላይ ንግዶችን ወደ መደበኛ መስመር ማስገባት እና በባህላዊ የግብርና ምርቶች (ማለትም ቡና፣ ሰሊጥ እና ጫት) ላይ ብቻ ያለውን ጥገኝነት በመቀነስ እንደ ቱሪዝም፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ ትራንስፖርት እና ሙያዊ አገልግሎቶች ያሉ የኤክስፖርት ዘርፎችን ማስፋፋትንም ሰነዱ በግብነት አካቷል።

በተጨማሪም በቆዳ፣ ጨርቃጨርቅ እና አግሮ-ኢንዱስትሪ ምርቶችላይ እሴት በመጨመር በዓለም ዓቀፍ እሴት ሰንሰለት ውስጥ መሳተፍን፣ የመንግስት እና የግል አጋርነትን ማጠናከርን፣ የኤሌክትሮኒክስ ንግድ እና የዲጂታል ንግድ ድንጋጌዎችን በስምምነቶች ውስጥ ማካተትን፣ እንዲኹም የፈቃድ አሰጣጥ እና የጉምሩክ አሰራርን ሙሉ በሙሉ ዲጂታላይዝ ማድረግንም መያዙን እንደራሴ ከሰነዱ ተመልክታለች።

በተያያዥነትም ፖሊሲው የፆታ እኩልነትን ማሻሻል፣ ከፍተኛ የምጣኔ ሀብት እድገትን ለማስመዝገብ እና አገራዊ ስትራቴጂክ የልማት ግቦችን ለማሳካት ወሳኝ መሆኑን ከመጥቀሱ ባለፈ፣ ሴቶች ሥራ ፈጣሪ በሆኑባቸው እና በሴቶች በሚመሩ የንግድ ዘርፎች እና ምርቶች ላይ የተሻለ የታሪፍ ጥበቃ እንዲያገኙ ምቹ ኹኔታ መፍጠርን ግቡ አድርጓል። አብዛኛው መደበኛ ያልሆኑ የድንበር ላይ ንግዶች በሴቶች የሚከናወኑ በመሆናቸው የንግድ ወጪዎችን በመቀነስ መብቶቻቸው ወደሚጠበቁባቸው መደበኛ የሥራ ዘርፎች እንዲገቡም ሰነዱ በግብነት አስቀምጧል።

በአየር ንብረት ለውጥ ዙሪያም ሰነዱ ሲያብራራ፣ ከአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት ማዕቀፍ ጋር በተጣጣመ መልኩ የተፈጥሮ ሀብት፣ የብዝሓ ሕይወት እና ሥነ-ምኅዳር ጥበቃን ከግምት ውስጥ ያስገባ የማምረት ሥርዓት መገንባትን፣ በ2011 የወጣውን የአሰሪ እና ሰራተኛ ዐዋጅ መሰረት በማድረግ የሠራተኞችን መብት ማስጠበቅ፣ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን መከልከል እና የሰው ኃይል ክህሎትን

በቴክኒክና ሙያ ማሳደግን፣ በመንግስት ግዥ ሥርዓት ውስጥ በአካል ጉዳተኞች ባለቤትነት የተያዙ ድርጅቶች የሚሳተፉበትን እና ምቹ የሥራ አካባቢ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸትን እንዲኹም ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የቁጥጥር መስፈርቶችን በቀላሉ እንዲያሟሉ የቴክኒክ እና የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን እገዛ ማድረግ እና የንግድ ወጪያቸውን መቀነስን የሚሉ ዝርዝር ያሉ ነጥቦችንም ይዟል።

በመጨረሻም የፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስልት እና ተቋማዊ ኃላፊነትን በማስቀመጥ የሚኒስትሮች ምክር ቤትን የፖሊሲ ማውጣት ሥልጣን፣ የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርን፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን እና የፕላን እና ልማት ሚኒስቴርን ዋና ፈጻሚ አካላት አድርጎ መለየትን፣ የትግበራ ጊዜ ሰሌዳን በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ መደብ መለየትን፣ እንዲሁም የንግድ ምክር ቤት እና የዘርፍ ማህበራት ማቋቋሚያ ዐዋጅ ቁጥር 341/1995፣ የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ዐዋጅ ቁጥር 813/2006፣ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንብ እና የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ማርኬቲንግ ደንብን የመሳሰሉ የሕግ ማዕቀፎችን ለማሻሻል ዕቅዶች መያዛቸውንም ከሰነዱ ተመልክተናል።

## 6.3 ክርክሮች እና ተግዳሮቶች

ከላይ እንደነሳነው፣ ይኽ ታሪካዊ ሰነድ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከመጽደቁ በፊት ከተለያዩ ነገረ-ጉዳዩ ይመለከተናል ካሉ ወገኖች በኩል ሰፋ ያሉ ክርክሮች እና ቅሬታዎች ባለፉት ሦሥት ዓመታት ሲሰሙ ተስተውሏል። የፖሊሲው ሂደት የተጀመረው ወጥ የሆነ የንግድ ማዕቀፍ አስፈላጊነትን በገለጸ የምርመራ ጥናት ሲሆን፣ በመቀጠልም የንግድ ምክር ቤቶችን፣ የንግድ ድርጅቶችን እና የዘርፍ ማኅበራትን ያካተተ የባለድርሻ አካላት ምክክር ሲደረግ ቆይቷል።

በዚኽ ሂደት ላይ ከተሰሙት እና ሊጠቀሱ ከሚችሉ የክርክር ድምጾች አንዱ፣ የኢ-መደበኛ ንግድ፣ የሕግ ማሻሻያዎች እና የነፃ ገበያ መርሆዎችን የተመለከተው ነበር። አብዛኛውን የኅብረተሰብ ክፍል በሚቀጥረው የኢ-መደበኛ ንግድ ዙሪያ በተነሳው በዚኽ ሙግት፣ የኢ-መደበኛ ነጋዴዎችን በግድ ወደ መደበኛ መስመር ማስገባት ኑሯቸውን ክፉኛ ያናጋዋል የሚለው ነጥብ ነበር። ፖሊሲው አዳዲስ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ማቋቋምን ቢያስቀምጥም፣ ተቺዎች ግን ነባሮቹን ማጠናከር የበለጠ ውጤታማ ይሆናል ባዮች ናቸው። ከዚኽ ባለፈም፣ ፖሊሲው በተመረጡ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ላይ የትርፍ ህዳግን ጨምሮ የተወሰኑ ቁጥጥሮችን ለመጣል ማሰቡ፣ በተቺዎቹ ዘንድ እንዲኽ ያሉ እርምጃዎች ከነፃ ገበያ መርሆዎች ጋር ይጣጣማሉ ወይ የሚል ጥያቄ እንዲነሳ ማድረጉን እንደራሴ ካደረገችው ዳሰሳ መረዳት ችላለች።

የሰነዱ አርቃቂዎች በበኩላቸው፣ የኢትዮጵያ መደበኛ የንግድ ፖሊሲ ማጣት የዓለም ዓቀፍ ገበያ ተደራሽነትን ያደናቀፈ እና የውጭ መዋዕለ-ንዋይ ፍሰትን የገደበ ከመሆኑ ባለፈ፣ የፖሊሲ ክፍተቱ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ያገደ ከመሆኑም በላይ ኢትዮጵያ ከግብርና ወደ ማኑፋክቸሪንግ እና አገልግሎት ዘርፍ እንዳትሻገር በማድረግ በዓለም ዓቀፍ የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ያላትን ተፅዕኖ መወሰኑን በማንሳት፣ ከነጻ ገበያው መርሆዎች ጋር ሰነዱ እንደማይላተም ተከራክረዋል።

ሌላይኛው ዋንኛ መከራከሪያ ነጥብ የነበረው፣ የውጭ ካፒታል ዕድሎች፣ ስጋቶች እና የመሠረተ ልማት አቅዶች ላይ ያሉ ገደቦችን የተመለከተው ነበር። ፖሊሲ አውጪዎቹ፣ የውጭ ካፒታልን ለመሳብ፣ የወጪ ንግድ ዕድሎችን ለማስፋፋት እና ምርታማነትን ሊያሻሽል የሚችል ውድድርን ለመፍጠር ሰነዱ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው ይጠቅሳሉ። ተቺዎቹ በበኩላቸው፣ በአዳዲስ ዘርፎች የሥራ ዕድል የመፈጠር አቅም እንዳለ ቢያምኑም፣ ድንበር-ዘለል የንግድ ተቋማት በጣም በፍጥነት ወደ አገር ውስጥ ከገቡ የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ሊቸገሩ እንደሚችሉ ይጠቅሳሉ። ለውጭ ገበያ መዋዠቅ በከፍተኛ ኹኔታ መጋለጥ አለመረጋጋትን ሊፈጥር እንደሚችል እና ከሊበራላይዜሽኑ የሚገኘው ጥቅም በአግባቡ ካልተከፋፈለ እኩልነት ማጣትን የመሰሉ የበረቱ ልዩነቶች ሊሰፉ እንደሚችሉም ስጋታቸውን ያስደምጣሉ።

የፖሊሲው አርቃቂዎች፣ እነዚህን ተግዳሮቶች ለመቀነስ መንገዶችን፣ የባቡር መስመሮችን እና የኃይል መሠረተ ልማቶችን ለማሻሻል መታቀዱን በመግለጽ፣ ይኽም የንግድ ድርጅቶች እየጨመረ የመጣውን የንግድ ፍሰት በብቃት እንዲያስተናግዱ ያስችላቸዋል ሲሉ ይሟገታሉ። በሠራተኛ ኃይል ሥልጠና ላይ መዋዕለ-ንዋይን በማፍሰስ፣ ለድንበር ተሻጋሪ ግብይቶች የፋይናንስ መሣሪያዎችን ለማልማት እና የአገር ውስጥ ፈጠራዎችን ለማበረታታት ጠንካራ የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ሕጎችን በተያያዥነት እንደሚወጡ በማንሳት፣ ፖሊሲው ይፈጥረዋል ተብሎ የተሰጋውን ተግዳሮት ማለፍ እንደሚቻልም ይጠቅሳሉ። አዲሱ ፖሊሲ፣ ይበልጥ ተገማች የሆነ የገበያ ተደራሽነት እና የክርክር መፍቻ ሥርዓቶችን ሊያስገኝ ቢችልም፣ አንዳንዶች ግን ትናንሽ የአገር ውስጥ ድርጅቶች በማይመጥኑት ፍጥነት ትልልቅ የውጭ ተዋናዮች በሩን እንዲከፍትላቸው ሊያደርግ ይችላል የሚለውን ስጋታቸውን ሲያነሱ ተሰተውሏል።

የሸማቾች ደህንነትም ሌላው፣ በሰነዱ ዙሪያ ሊነሳ የሚችል የክርክር ነጥብ ነው፤ ምክንያቱም ፖሊሲ አውጪዎች እጅጉን የናረ ዋጋ ማውጣትን ለመከላከል፣ የምርት ደህንነትን ለማረጋገጥ እና የጥራት ደረጃዎችን ለመጠበቅ ቢሹም፣ ፈጣን ሊበራላይዜሽን እንዲኖር የሚፈልጉ ወገኖች በበኩላቸው፣ ከመጠን በላይ ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድ መዋዕለ-ንዋይን ሊያደናቅፍ እና ተወዳዳሪነትን ሊቀንስ እንደሚችል ያስጠነቅቃሉ።

የፖሊሲው ተሟጋቾች፣ ግልጽ የሕግ መመሪያዎች መኖራቸው ኢትዮጵያ በዓለም ዓቀፍ ባለሀብቶች ዘንድ ያላትን ስም እንደሚያሳድግ እና የአገር ውስጥ ሥራ ፈጣሪዎች አቅማቸውን እንዲያሳድጉ እንደሚያበረታታ ይናገራሉ። በአንጻሩ ተቺዎቹም፣ ፖሊሲው እንደሚያልመው ወደ ክፍት ገበያ የሚደረገው ሽግግር በአግባቡ ካልተመራ እኩልነትን ሊያባብስ ወይም አዳዲስ በማደግ ላይ ያሉ ኢንዱስትሪዎችን ሊጎዳ ይችላል ሲሉ ያስጠነቅቃሉ።

እንደእነዚኽ ወገኖች ሙግት፣ የአገር ውስጥ አነስተኛ እና መካከለኛ ነጋዴዎች ግዙፍ ካፒታል እና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ይዘው ከሚገቡት የውጭ ኩባንያዎች ጋር እኩል የመወዳደር አቅም ስለሌላቸው፣ የመውደቅ አደጋ እንዳይገጥማቸው መንግስት የገንዘብ እና የቴክኒክ ድጋፍ ሊያደርግላቸው እንደሚገባም ያሳስባሉ።

እንደ የተባበሩት መንግሥታት የንግድ እና ልማት ጉባኤ ያሉ ተቋማት ይኽንን እርምጃ ኢትዮጵያ በ50 ዓመታት ታሪኳ ውስጥ ያደረገችው ትልቁ የንግድ ዘርፍ ሊበራላይዜሽን አድረገው ከማወደስ ባለፈ፣ ይኽ አዲስ ፖሊሲ ለዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት የምታደርገውን ጥረት እንደሚያፋጥነው ሲያነሱ፤ ስጋት አለብን ባዮቹ በበኩላቸው፣ የአገር ውስጥ የንግድ ዘርፍ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ዜጎች የስራ ዕድል የፈጠረ በመሆኑ፣ የውጭ ኩባንያዎች በቴክኖሎጂ የተደገፈ አሰራር ይዘው ሲመጡ በተዘዋዋሪ የስራ አጥነት ጫናን ሊያሳድር እንደሚችል ስጋታቸውን ሲገልጡ ተስተውሏል።

በሌላ በኩል፣ ይኽ ውድድር የአገር ውስጥ ነጋዴዎች አሰራራቸውን እንዲያዘምኑ፣ ዲጂታል የክፍያ ሥርዓቶችን እንዲለምዱ እና ከዓለም ዓቀፍ አቅራቢዎች ጋር የጋራ አጋርነት በመፍጠር እንዲያድጉ ዕድል ይሰጣል ቢባልም፤ የንግድ በሩ ሙሉ በሙሉ ክፍት መደረጉ ከወጪ ንግዱ በበለጠ የገቢ ዕቃዎች እንዲበራከቱ ሊያደርግ ይችላል፤ ይኽም በአገሪቱ የክፍያ ሚዛን ላይ የአጭር ጊዜ ቢሆን ጫና ሊፈጥር ይችላል የሚለውን ስጋትም አለማንሳት የሚቻል አይመስልም።

የምጣኔ ሀብት ተንታኞች እንደሚሉት፣ ኢትዮጵያ ለዘመናት ጥሬ ቡና እና የቅባት እህሎችን ብቻ በመላክ ከምታገኘው አነስተኛ የውጭ ምንዛሬ እንድትላቀቅ ይኽ ፖሊሲ ትልቅ መሠረት ይሰጣል። የውጭ ኩባንያዎች መግባታቸው የአገሪቱን ምርቶች ጥራት በማሻሻል፣ ኢትዮጵያ በዓለም ዓቀፍ ገበያ ላይ ያላትን ተወዳዳሪነት ያሳድገዋልም ቢሉም፣ የውጭ ድርጅቶች በቡና፣ በጫትና በቅባት እህሎች የወጪ ንግድ ላይ በቀጥታ እንዲሰማሩ መፈቀዱ የውጭ ምንዛሬ ግኝቱን ሊያሳድገው ቢችልም፣ እንደ ቡና ባሉት ምርቶች ላይ ያለው የዓለም ገበያ ዋጋ ሲቀንስ፣ የአገሪቱ ገቢ አሁንም ለቀውስ ተጋላጭ ሆኖ ሊቀጥል ስለሚችል ፈጠን ባለ ኹኔታ ወደ ማኑፋክቸሪንግ መሸጋገር ወሳኝ መሆኑን ጠንከር አድርገው ይከራከራሉ።

## 6.4 የብሪጅ ምክረ-ሐሳቦች

ከላይ በዳሰሳችን የተመለከትነው ባለ 48 ገጹ አዲስ ታሪካዊ የንግድ ፖሊሲ፣ እንደውም ዘግይቷል ከሚሉት ድምጾች ጋር ተቋማችን ብትሰለፍም፣ ፖሊሲው እንደለመው የኢትዮጵያን የንግድ ሥርዓት የተሳለጠ እና ኢኮኖሚውንም ወደፊት የሚያስጉዝ እንዲሆን፣ ቀጣዮቹን አጠር ያሉ ምክረ-ሐሳቦች ብሪጅ ማንሳት ትሻለች፤

* የውጭ ባለሀብቶች በችርቻሮ እና በጅምላ ንግድ ላይ ሲሰማሩ ሊፈጠር የሚችለውን የኮንትሮባንድ፣ የትይዩ ገበያ እና የዋጋ ማጭበርበር ለመቆጣጠር፣ የኢፌድሪ የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጠንካራ የክትትል መዋቅር መዘርጋት እንዳለበትም ብሪጅ ማሳሰብ ትሻለች። አዲሱን የፖሊሲ ትግበራ ተከትሎ ሊከሰቱ የሚችሉትን እንደ ሕገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር፣ የታክስ ማጭበርበር እና የኮንትሮባንድ ንግዶችን ለመቆጣጠር ይኸው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ያለውን የዲጂታል እና የሰው ኃይል አቅም በተገቢው ፍጥነት ከኩነቶቹ ጋር አስተሳስሮ ሊያዳብር እንደሚገባም ማስታወስ ያስፈልጋል።

* ሌላይኛው ምክረ-ሐሳባዊ ነጥባችን ከቢሮክራሲያዊ ማነቆዎች ጋር የተሳሰረ ነው። ምንም እንኳን ባለፉት ጥቂት ዓመታት የቢሮክራሲው ማናቆ ቀስ በቀስ ለውጦችን ቢያስመዘግብም፣ እንደ የተባበሩት መንግሥታት የልማት ጉባኤ ያሉ ተቋማት ቀሪ የቤት ሥራዎች መኖራቸውን ይጠቅሳሉ። እናም፣ ፖሊሲው እንደስቀመጠው ምቹ የንግድ ከባቢን ለመፍጠር የጉምሩክ አሰራር ዲጂታላይዜሽን ፍጥነትን መጨመር እና የፈቃድ አድሳት መዘግየቶች የመሳሰሉ ቢሮክራሲያዊ ማነቆዎች ካልተቀረፉ አዲሱ ፖሊሲ ያቀደውን የመሥራት ምቹነት ሙሉ በሙሉ ማሳካት ሊቸግር ይችላልና በቅጡ ቢታሰብበት እንላለን።

* የንግድ ፖሊሲው፣ ከአገሪቱ የግብርና፣ የኢንዱስትሪ እና የፋይናንስ ፖሊሲዎች ጋር በተሟላ ኹኔታ ተናቦ በፍጥነት ሥራ ላይ ካልዋለ የሚፈለገውን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል መገመት ብዙም አስቸጋሪ አይሆንም። በተለይም በዚኹ ጉዳይ በቀጥታ የሚመለከተው የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት፣ ይኽንን ጉዳይ በተቻለ ፍጥነት ይከውነው ዘንድ ብሪጅ ማሳሰብ ትሻለች።

## 6.5 ምክረ-ሐሳቦች ለሕዝብ ተወካዮቹ

እንደሚታወቀው፣ ይኽች የብሪጅ የእንደራሴ ዕትም፣ ምንም እንኳን የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን በሳምንታዊ ምልከታዋ ብትዳስስም፣ ዋንኛ ትኩረቷ የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መሆኑን፣ ወርኻዊ አንባቢዎቻችን ያስታውሳሉ ብለን እናምናለን። ከዚኽ አኳያም፣ እንደራሴ ቀጣዮቹን ምክረ-ሐሳቦች ለሕዝብ ተወካዮቹ ማቅረብ ትሻለች፦

ከላይ ያቀረብነው ዳሰሳ እንደሚያሳየው፣ አዲሱ ፖሊሲ በግብነት ያስቀመጣቸውን የዐብይ ኢኮኖሚ ትልሞች ማሳካት የሚቻለው፣ ለበርካታ ዓመታት ሥራ ላይ የነበሩት እና ተበታትነው የቆዩት ሕግጋት ሲሻሻሉ እና ተያያዥ ርዕሰ-ጉዳዮችም በቅጡ ሲታሰብባቸው ብቻ ነው። በመሆኑም ምክር ቤቱ የሚከተሉትን የሕግ አውጪነት ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነቶቹን ቅድሚያ ሊሰጥባቸው ይገባል፦

**ሀ፦ የቆዩ ዐዋጆችን በአስቸኳይ ማሻሻል፦**

በሰነዱ ላይ የተጠቀሱትን የንግድ ምክር ቤት እና የዘርፍ ማኅበራት ማቋቋሚያ ዐዋጅ ቁጥር 341/1995 እና የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ ዐዋጅ ቁጥር 813/2006ን፣ ከሊበራላይዜሽን እና ከዲጂታል ንግድ ሥርዓት ጋር እንዲጣጣሙ ተደርገው ሊሻሻሉ እንደሚገባ የዳሰስነው ራሱ የንግድ ፖሊሲው ሰነድ ይጠቅሳል፤ እናም፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቱ እነኚን ማሻሻያ ያስፈልጋቸዋል ተብለው የተጠቀሱትን ነባር ዐዋጆች ቢቻል ተሰናባቹ ምክር ቤት ባሉት ቀሪ ሳምንታት ያሻሽላቸው ዘንድ ብሪጅ ማሳሰብ ትፈልጋለች።

**ለ፦ የሥርዓተ-ፆታ እና የቅጥር ዋስትና ዐዋጅ አስፈላጊነት፦**

ይኸ የፖሊሲ ሰነድ፣ በንዑስ አምስት እንደሚያትተው፣ የሴቶችን የንግድ እና ምጣኔ ሀብታዊ ዐቅም ማጎልበትን ግቡ ያደርጋል፤ ከዚያ ባለፈም፣ ከላይ አጠር አድርገን ስለ ሰነዱ እንዳነሳነው፣ ኢ-መደበኛ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ወደ መደበኛው ንዑስ ኢኮኖሚ ማካተት አንዱ የሰነዱ ግብ ሆኖ ተቀምጧል። ከዚኽ አንጻር ስንመለከተው፣ አብዛኛው የኢ-መደበኛ ንግድ ውስጥ ሴቶች በስፋት እንደመሳተፋቸው፣ እነዚህን ይዘው የነበሩ ንግዶች ፖሊሲው እንደተለመው ወደ መደበኛው የንግድ መስመር ሲገቡ የሴቶችን መብት፣ የቅጥር ዋስትና እና የታሪፍ ጥበቃ የሚያረጋግጥ/ጡ ዐዋጅ/ጆችን ምክር ቤቱ ቢያስብበት ስትል ምክረ-ሐሳቧን ታቀርባለች።

**ሐ፦ ጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓት፦**

ፖሊሲው እንደሚያመለክትውም ሆነ፣ የንግድ ፖሊስ ከመሆኑ አኳያ ቀጥተኛ ኃላፊነቱም ሆነ ፈጻሚነቱ ለንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት እንደሆነ ራሱ ሰነዱ ጭምር እንደመጥቀሱ፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በተለይም ይኽ ጉዳይ በቀጥታ ይመለከታቸዋል በሚላቸው ቋሚ ኮሚቴዎቹ በኩል፣ የፖሊሲዉን ተፈጻሚነት የሚከታተልበት ለየት ያለ የቁጥጥር ሥርዓት ቢዘረጋ፣ ለፖሊሲው ተፈጻሚነት የሚኖረው ፋይዳ ብዙ ነውና ምክር ቤቱ በአጽንዖት ቢመለከተው ማለትም እንሻለን። በተለይም፣ ላይኛው የምክረ-ሐሳብ ነጥባችን ላይ፣ የውጭ ባለሀብቶች በጅምላ እና ችርቻሮ ንግድ ላይ በቀጥታ እንዲሰማሩ መፈቀዱ የኮንትሮባንድ፣ የትዩዩ ገበያ እና ዋጋ አሳንሶ የመላክ/አስበልጦ የማስመጣት አደጋ እንዳይፈጥር በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የክትትል መዋቅር እንዲዘረጋ ጠቅሰናል፤ እናም፣ እነዚኽ በመሥሪያ ቤቱ የሚዘረጉ

የክትትል መዋቅሮችን፣ ምክር ቤቱ ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ ግምገማውን ሲያከናውን፣ ይኽንን ርዕሰ-ጉዳይ በአትኩሮት ቢመለከተው ለፖሊሲው ኹለንተናዊ ትግበራ ጠቀሜታው ብዙ መሆኑን አበክረን ማስታወስ እንፈልጋለን።

## ፍካሬ ዘ እንደራሴ

“እንደራሴ” የሚለው ንባበ-ቃል በኢትዮጵያ ጥንታዊ እና ዘመናዊ የፖለቲካ ተዋስዖ እና የሥነ-መንግሥት ታሪክ ውስጥ ግዝፈት የነሳ ፍካሬያዊ ንባበ-ቃል ነው። የቃሉ ከየት መጥነት እና ፍካሬም፣ በአጠቃሎ መልኩ ይኽን መሰል ፍቺዎች ነበሩት/አሉትም።

ንባበ-ቃሉ የተገኘው “እንደ” እና “ራሴ” ከሚሉ የኹለት ቃላት ጥምረት ነው። “እንደ”፦ መስያ፣ ፈንታን ወይም ምትክን ሲያመለክት፤ “ራሴ”፦ ራስ ጠሪውን ማንነት አልያም ባለቤቱን-ሲፈከርም ባለሥልጣኑን ያነጽራል። በአማሪያዊ ፍቺውም፣ “እንደ እኔ” ወይም “እኔን ሆኖ” ማለት ነው ይሏል። በኢትዮጵያ ሥነ-መንግሥት ታሪክ “እንደራሴ” የሚለው ማዕረግነቱን ሲያጣቅስ፣ በተለያዩ ዘመናት የተለያየ ማኅበረ-ፖለቲካዊ ትርጓሜ ነበረው፤ ለማሳያ፦

ሀ- የንጉሠ ነገሥቱ ተወካይ (በፈረንጅ አፍ- Regent እንዲሉ)፦ በንጉሣዊው ሥርዓት ዘመን ንጉሠ ነገሥቱ በአንዳች ምክንያት (ለዐቅመ-መንበር ባለመድረስ፣ በሕመም ወይም በሌላ ምክንያት) አገረ-መንግሥቱን መምራት ካልቻሉ፣ ሙሉ ሥልጣን ተሰጥቶት አገሪቱን የሚያሥተዳድረው ሰው “ቢትወደድ-እንደራሴ” ይባል ነበር።

ለ- የአካባቢ ወይም የክፍለ-ሀገር ገዢነት፦ ንጉሠ ነገሥቱ በየክፍለ ሀገራቱ ‘ራሳቸው ዘወትር መገኘት ስለማይችሉ፣ በ‘ርሳቸው ስም የሚፈርዱ እና የሚያሥተዳድሩ ተወካዮቻቸውን “እንደራሴ” ይሏቸዋል፤ ይኽም የንጉሡ ምሉዕ ተወካይነትን ይሰጣል።

ሐ-የሕዝብ እንደራሴነት፦የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ከመጣ ወዲኽ ግን ቃሉ አዲስ ፍካሬ ያዘ። ሕዝቡ በ‘ራሱ ፈንታ ሆኖ በምክር ቤት እንዲመክርለት እና ውሳኔም እንዲሰጥለት የሚመርጣቸው ሰዎች “የሕዝብ እንደራሴዎች” መባል ጀመሩ። የዚኽ ፍካሬም፣ “ሕዝቡን ሆኖ የሚሠራ”፣ “ምስለ-ሕዝብ” አልያም “የሕዝቡ ተወካይ” የሚል ትርጓሜን አሰጠው።

ዛሬ “ተወካይ” (በምዕራቡ የምክር ቤት ታሪክ ጅማሮ-Representative-እንዲሉ) ከሚለው ቃል ጋር መሳ ለመሳ ሆኖ ያገለግላል። ሆኖም “እንደራሴ” የሚለው ቃል ከውክልና ባለፈ፣ የወከለውን አካል ሙሉ ክብር እና ማንነታዊ ተዛምዶ ይዞ የሚገኝ ክብደት ያለው ፖለቲካዊ እና ማኅበረ-ባህላዊ ፍካሬ አለው።

## የብሪጅ አፈካከር

ተቋማችን ብሪጅ፣ የአማርኛን ሰዋስው ደንብ ጠብቃ፣ ይኽንን ቃል ከኋለኛው ወደዚኽ ዘመን አናጥቃ በመፈከር ተጠቅማለች። አስቀድመን ሊቃውንቱ ያስቀመጡትን እንጥቀስ፤ ደስታ ተክለ ወልድ፣ እንደ ራሴ፣ እኔን ሆኖ፣ የእኔን ሥልጣን ይዞ የሚሠራ ብለው ሲፈቱት፤ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ በፈንታ፣ በምትክ የሚቆም ሲሉት፤ ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጸው በተራቸው፣ ተለዋጭ፣ ተወካይ፣ ባለሙሉ ሥልጣን የሚል ፍቺ ይሰጡታል። ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀልም ቢሆኑ፣ አንድ ሰው በራሱ ስም ሳይሆን በሌላው ስም ተገኝቶ የሕግ ተግባራትን ሲያከናውን እንደራሴ መባሉን ያነሳሉ። እነዚኽ ዋቢዎች እንደሚያሳዩት፣ ቃሉ በመጀመሪያ ለነገሥታት ተወካዮች ብቻ ይሠራበት የነበረ ሲሆን፣ ኋላ ለሕዝብ ተወካዮች እንዲሠራበት የተደረገው የሕዝቡን ልዕልና ለመግለጽ ውለዋል፤ አለፍ ሲልም፣ ተወካዩ ሕዝቡን ሆኖ ይገኛል፤ እንደ ሕዝቡ ሆኖ ይጠራል የሚለውን ፍካሬ ይሰጣሉ።

በዚኽ አግባብ፣ “እንደራሴ” ስንል፦ አንድም ራስ የሚለውን የኢትዮጵያ ፌዴሬሽን ከቆመበት ‘የራስን ዕድል በራስ የመወሰን’ ሕገ-መንግሥታዊ ነባር መርህ ጋር አናጽረን ፈክረነዋል። ይኽ ማለት፣ በዚኽ መርህ ውስጥ ያለው ‘ራስ’፣ የሚለው ትርጉም የሚጠቅልላቸውን ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች፣ በ “እንደራሴ” ውስጥ ያለውን ‘ራሴ’ን ለመፍታት ፍካሬያዊ ትርጓሜን ተጠቅመናል። ከዚያ ባለፈም፣ በቀደመው ዘመን መራጩ ንጉሠ ነገሥቱ እንደሆነው ሁሉ፣ በዚኽኛው የእኛው ዘመን ሕዝብ ነውና፣ “እንደራሴ” ስንል፦ እንደ መረጠው ሕዝብ፣ ብሔረሰብ አልያም ብሔር የሆነ በሚል ፍቺ መጠቀማችንን ልብ ይሏል። በዘመናዊው የምርጫ ሥርዓት ስናነጽረውም፣ መራጩ ግለሰብ እንደራሴውን ‘ተናገር በከንፈሬ፣ ተቀመጥ በመንበሬ’ ሲል፣ በነገረ-ሕይወቱ ይወስንለት ዘንድ ወደ ምክር ቤቱ መርጦ ይልከዋል። የመረጠውም እንደራሱ ካልሆነለት፣ ምስለ እኔነቱን ሊነጥቀው መቻሉን ያስረግጣል።

የ“እንደራሴ” ንባበ-ቃል፣ ምንም እንኳን የመጀመሪያው የኢትዮጵያ የእንደራሴዎች ምክር ቤት ሲቋቋም፣ የምክር ቤቱ የሥራ ቋንቋ በዘመኑ ብሔራዊ ቋንቋ የነበረው አማርኛ ብቻ ቢሆንም ቅሉ፣ ንባበ-ቃሉ ግን በሌሎቹ የአገራችን የብሔር ብሔረ ሰቦች ቋንቋዎች ውስጥም መገኘቱን ልብ ይሏል፤ ለማሳያ፦ በሲዳማ- amaalete mina፣ በአፋን ኦሮሞ-Bakka bu’aa፣ በትግሪኛ- ከማይ፣ በወላይተኛ Kal Ati-ya/Taga ton መባሉን ያስታውሷል።

**ከራስ ውርድ፦**

“በእነዚኽ ወርኃዊ የእንደራሴዎቹ ጥቅንሮች ውስጥ ያሉት ኹሉም የገጸ-ሰብ እና የገጸ-መስኮች ምስሎች የተገኙት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ይፋዊ የመረጃ ምንጮች ነው፤ እንዲኹም፣ ኹሉም ቁጥራዊ ዘገባዎች የተወሰዱትም ከዚኽ ምንጭ ነው። ዳሰሳዊ ምልከታዎቹ፣ አጠቃሎዎች እና ተያያዥ ትንታኔዎቹ የተቋማችን ናቸው።”

# እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።


BRIDGE Research & Innovation for Democratic Governance and Enhanced Peace

+251 115 57 74 96

+251 99 808 5013

info@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, O ce No. 5, Addis Ababa.